በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር

# በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር

ለ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሁሴን አህመድ ሁሴን

ሰኔ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር

ለ በተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ

በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ሁሴን አህመድ ሁሴን


ሰኔ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር

በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር

በ

ሁሴን አህመድ ሁሴን

ሰኔ 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| <u>ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)</u> | ____________________ |
| አማካሪ | ፊርማ |
| <u>ታደሰ ሲባሞ (ዶ/ር)</u> | ____________________ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| <u>ጌታቸው አዱኛ (ዶ/ር)</u> | ____________________ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን የትምህርት እድል ለሰጠኝ ለጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፤ ለአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን እና ሁለተኛ አመት የኮሌጅ ተማሪዎች ለጥናቴ መረጃ በመስጠት ስለተባበሩኝ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ከዚህ በመቀጠል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምርምሬን በገንዘብ ስለደገፈኝ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

በተጨማሪም የሁለተኛ ዲግሪዬን ስማር ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የአማርኛ ተግባራዊ ስነልሳን መምህራን በሙሉ በሁለት አመቱ የትምህርት ወቅት ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ሁሉ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ። በተለይም ደግሞ የምርምር ጥናቴን በማንበብና የምርምር አቅጣጫ በመጠቆም፣ የተበላሸውን በማስተካከል ከኔው ጋር እኩል ለደከምከው አማካሪዬ ለዶ/ር ግርማ ገብሬ ከፍተኛ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም በሁለት አመት የትምህርት ቆይታዬ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትዪ ልጆቼን በመንከባከብና በማስተማር ትልቅ ኃላፊነት ለተወጣሽው በጣም ለምወድሽ ባለቤቴ ቆንጂት ከበደ ውድነህ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርብልሻለሁ። እንድሁም ፍቅር ለሆናችሁ ልጆቼ ለመስዑድ ሁሴን፣ ለአሚር ሁሴን፣ ለዘምዘም አለሙ፣ ለዮናስ ተስፋዬ በጣም እወዳችኋለሁ። አመሰግናለሁ። በተጨማሪም በወጣሁ በገባሁ ቁጥር ጥሩ ነገር እንዲገጥመኝ ለምትመኝልኝና ለምትመርቀኝ የአንተን አባትነት በልጆቼ እንዳይ ላደረከኝ አባቴ አህመድ ሁሴን አሊ ረጅም እድሜና ጤና እንዲሰጥህ እየተመኘሁ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v
አጠቃሎ ........ vi
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ........ 2
1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.6 የጥናቱ ውስንነት ........ 4
ምዕራፍ ሁለት ........ 5
ክለሳ ድርሳን ........ 5
2.1 ንድፈ-ሀሳባዊ መሠረቶች ........ 5
2.1.1 የጽህፈት ክሂል ምንነት ........ 5
2.1.2 የጽህፈትን ክሂል ማስተማር የሚያስገኘው ጥቅም ........ 6
2.1.3 የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦዎች ........ 7
2.1.3.1 የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን ........ 7
2.1.3.2 ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊ እና አዕምሯዊ ባህሪያት ........ 8
2.1.4 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦች ........ 10
2.1.4.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ ........ 10
2.1.4.2 ሂደታዊ አቀራረብ ........ 11
2.1.4.2.1 ቅድመ ጽህፈት ........ 12
2.1.4.2.2 የጽህፈት ጊዜ ........ 12
2.1.4.2.3 ድህረ ጽህፈት ........ 13
2.1.5 የጽህፈት ክሂል መልመጃ አይነቶች ........ 14
2.1.5.1 ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ ........ 14

2.1.5.2 ጠቋሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃ 15
2.1.5.3 ልቅ የጽህፈት ክሂል መልመጃ 15
2.1.6 ለመፃፍ የሚያነሳሱ ተግባራት 16
2.1.6.1 ተግባራዊ የጽህፈት መለማመጃዎች 16
2.1.6.2 የስሜት መግለጫ ጽሑፎች 16
2.1.6.3 ትምህርት ቤት ተኮር የጽህፈት መለማመጃዎች 16
2.1.7 የውጤት አሰጣጥ መስፈርትና የማረሚያ ኮድ 17
2.1.8 የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ነጥቦች 18
2.1.8.1 የቃላት አመራረጥ 19
2.1.8.2 የአረፍተ-ነገር አወቃቀር 19
2.1.8.3 የስርዓ-ተነጥብ አጠቃቀም 19
2.1.8.4 የአንቀጽ አወቃቀር 20
2.1.8.4.1 የአንቀጽ አንድነት 20
2.1.8.4.2 የአንቀጽ ቅንብር /ውህደት/ 20
2.1.8.4.3 የአንቀጽ ተያያዥነት 20
2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 21
ምዕራፍ ሦስት 25
የአጠናን ዘዴ 25
3.1 የጥናቱ ንድፍ 25
3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች 25
3.3 የናሙና አወሳሰድ 26
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች 26
3.4.1 የጽህፈት ችሎታ መለኪያ ፈተና 27
3.4.1.1 የጽህፈት ፈተናው አዘገጃጀትና አቀራረብ 27
3.4.1.2 የጽህፈት ፈተናው አስተራረም 28
3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ 29
3.5 የመረጃ አተናተን 30
3.5.1 የጽህፈት መረጃ አተናተን 30
3.5.2 የጽሑፍ መጠይቅ አተናተን 31

ምዕራፍ አራት ........ 32
የመረጃ ትንተና ........ 32
4.1. የቃላት አጠቃቀም ........ 32
4.2. የአረፍተ-ነገር ሰዋሰዋዊነት ........ 39
4.3. የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ........ 47
4.4. የአንቀጽ አደረጃጀት ........ 53
4.5. በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የታየ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ........ 57
4.6. ተማሪዎች ለጽሕፈት ችሎታ ያላቸው ፍላጎት ........ 62
4.7. መምህራን ለጽሕፈት ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ........ 63
ምዕራፍ አምስት ........ 66
ማጠቃለያና አስተያየት ........ 66
5.1. ማጠቃለያ ........ 66
5.2 አስተያየት ........ 68
ዋቢ ጽሑፎች ........ 70
አባሪዎች
አባሪ “ሀ” በተጠኝ ተማሪዎች የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ናሙና
አባሪ “ለ” የተጠኝ ተማሪዎች የጽህፈት ፈተና ናሙና
አባሪ “ሐ” የድርሰት ማረሚያ መስፈርቶች
አባሪ “መ” አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች የፃፉት ድርሰት ናሙና
አባሪ “ሠ” አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች የፃፉት ድርሰት ናሙና

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሰንጠረዥ 1 ድርሰት እንዲጽፉ የተደረጉ ተጠኝዎች ብዛት ........................................ 27

ሰንጠዥ 2 ተጠኝዎች የፃፉትን ድርሰት ያረሙ መምህራን ዝርዝር .......................... 29

ሰንጠረዥ 3 የተጠኝዎች ቃላት አጠቃቀም ችሎታ .................................................. 32

ሰንጠረዥ 4 የተጠኝዎች ቃላት አጠቃቀም ችሎታ ከፆታ አንፃር .............................. 34

ሰንጠረዥ 5 ተጠኝዎች ለቃላት ምርጫን በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ............. 35

ሰንጠረዥ 6 የተጠኝዎች አረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ በፃፉት ድርሰት .................. 39

ሰንጠረዥ 7 የተጠኝዎች የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ ከፆታ አንፃር .................... 40

ሰንጠረዥ 8 ተጠኝዎች ለአረፍተ-ነገር አወቃቀር በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ... 41

ሰንጠረዥ 9 የተጠኝዎች ስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም በፃፉት ድርሰት ........................... 47

ሰንጠረዥ 10 የተጠኝዎች ስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ከፆታ አንፃር ............................. 49

ሰንጠረዥ 11 ተጠኝዎች ለስርዓተ-ነጥብ በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ........... 50

ሰንጠረዥ 12 የተጠኝዎች አንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች በፃፉት ድርሰት ................... 54

ሰንጠረዥ 13 የተጠኝዎች አንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ከፆታ አንፃር ....................... 55

ሰንጠረዥ 14 ተጠኝዎች ለአንቀጽ አደረጃጀት በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ..... 56

ሰንጠረዥ 15. የተጠኝዎች ፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም በፃፉት ድርሰት........................ 57

ሰንጠረዥ 16. የተጠኝዎች የፊደል ቅርጽ አጠቃቀም ችሎታ ከፆታ አንፃር................ 59

ሰንጠረዥ 17 ተጠኝዎች ለፊደል ቅርጽ አጠቃቀም በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ...59

ሰንጠረዥ 18 የድርሰት መፃፍ ፍላጎት በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ................. 62

ሰንጠረዥ 19 ተጠኝዎች ለጽህፈት መልመጃዎች እርማትና ማስተካካያ በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ….. ................................................. ……...63

ሰንጠረዥ 20 ተጠኝዎች ድርሰት ለመጻፍ ርዕስ መረጣን በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ.................................................................... 64

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዓቢይ አላማ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የሚማሩ የሁለተኛ ዓመት አማርኛ አፍፌትና ኢ-አፍፌት ተማሪዎች ያላቸውን የጽህፈት ችሎታ በንጽጽር ማጥናት ነው። ጥናቱንም ከግብ ለማድረስ አጥኚው በዋናነት መጠናዊ ምርምር የተጠቀመ ሲሆን በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር ተጠቅሟል። የመረጃ ምንጮች የሰነድ ፍተሻ፣ በተጠኚዎች የተፃፉ ድርሰቶችና የተሞሉ የጽሑፍ መጠይቆች ናቸው። መረጃዎቹም በቁጥር የመረጃ ትንተና በገላጭ ንድፍ አቀራረብ በንጽጽር ትንተና ተደርጎባቸዋል። ጥናቱም ጥቅል ንሞና ዘዴ በመጠቀም 31 በአማርኛ ትምህርት ክፍል ከሚማሩ አማርኛ አፍፌትና ኢ-አፍፌት የሁለተኛ አመት ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቧል። ከተጠኚዎቹም 11 ተማሪዎች አማርኛ አፍፌት ሲሆኑ 20 ተማሪዎች ደግሞ ኢ-አፍፌት ናቸው። ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በጥንቃቄ ከተተነተነ በኋላ የተገኘው ውጤት በቃላት አጠቃቀምና ምርጫ፣ በሰዋስው አጠቃቀም፣ በአንቀጽ አደረጃጀት፣ በፊደል ቅርጽ አጣጣልና አጠቃቀም አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች ከኢ-አፍፌት ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች ከአማርኛ አፍፌት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም የጥናቱ ግኝትን መሠረት በማድረግ ሁለቱም ቡድኖች ያላቸውን የክሂል ክፍተት እንዲያጠቡ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ በመሆን ተማሪዎች የግልና የቡድን ስራ እንዲሰሩ በማድረግ አንዱ ተማሪ ከሌላው እየተማረ የክሂል እውቀት ክፍተታቸውን የሚሞሉበትን መንገድ ማመቻቸት ቢችሉ የተሻለ ነው። እንዲሁም መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ጫና ሳይፈጥሩ ተማሪዎቹ በፈለጉት ርዕስ ላይ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያደርጉበትን መንገድ ቢያመቻቹ። መምህራን ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰቶች አይተው ችግራቸውን እንዲቀርፉ ግብረ-መልስ መስጠቱ ለተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂል ማደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የጽሕፈት ክሂልን በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ለተማሪዎች ከፍተኛ ችግር ከመሆኑም በላይ፣ ከመካከላቸው የክሂሉ ባለቤት ለመሆን የሚበቁት በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በእርግጥም፣ ጥሩ ድርሰትን መጻፍ መቻል ከባድ፣ አዝጋሚ ሂደት የሚታይበት፣ ብዙ ተማሪዎችን የሚያስጨንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው በማለት Richards (1990), Davies እና Widdowsen (1974) አብራርተዋል፡፡

ከላይ ምሁራኑ የገለጹት ሀሳብ የጽህፈት ክሂል ከባድና ረጅም ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡ በመሆኑም አጥኝው በምሁራኑ ሀሳብ ትክክለኛና ጥናቱንም የሚደግፍ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ መልኩ Richards እና Renandya (2002, 303) "ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋውን በሚገባ ተጠቅመው፣ ሀሳብ አሰባስበውና አዳብረው ለመፃፍ እንደሚከብዳቸው የማያጠራጥር ሀቅ ነው" በማለት ሀሳባቸውን ያጠናክሩታል፡፡ በሌላ በኩል Abiy (2013, 58) "ጽህፈትን በሁለኛ ቋንቋ ለማዳበር የአፍ መፍቻ ቋንቋ የጽህፈት ክሂል ትልቅ አስተዋጽኦ አለው" በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የጽህፈት ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር በቀጣይ በሁለተኛ ቋንቋና በውጭ ቋንቋ ለሚማሩት የጽህፈት ትምህርት መንገዱን ቀላል እንደሚያደርግላቸው ለማሳየት ነው፡፡

በመሆኑም ጥሩ የመጻፍ ክሂል፣ ለስነትምህርታዊ ብቃትና ለተሳካ ውጤት፣ ለተለያዩ ስራዎችና ሙያዎች እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ አስፈላጊና ጠቃሚ ክሂል በአማርኛ ቋንቋ ረገድ በአሁኑ ጊዜ ምን ይመስላል? ብለን ስንጠይቅ ክሂሉ በከፍተኛ ደረጃ የደከመ መሆኑን በውል ከምናስተውለው በተጨማሪ የተለየዩ ጥናቶችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ባየ (2000፣ XXVi) "…በየደረጃው እየተመረቁ የሚወጡት ተማሪዎች ተራ ዘገባ (ሪፖርት) ለማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት እንደሌላቸው ነው፡፡ ባጭሩ ሀሳብን አስተካክሎ በተስተካከለ አረፍተ-ነገር የመግለጽ ብቃት የላቸውም" በማለት የጽህፈት ክሂሉን መዳከም አብራርተዋል፡፡ እንዲሁም ተስፋዬ (1981) በህትመት ደረጃ አለቀላቸው ተብለው ለአንባቢ የሚሰራጩትም

ጽሑፎች (ጋዜጦች፣ መጽሄቶችና መጻህፍት) በርካታ ስህተት ይታዩባቸዋል በማለት ሀሳቡን ያጠናክራሉ፡፡ በአጠቃላይ፣ ዛሬ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን አስመልክቶ የተማሪዎችም ሆነ ሙያቸው አስገድዷቸው የሚጽፉ ፀሐፍት ጽሑፎች ደካማ እንደሆኑ ሌሎች ጥናቶችም አመላክተዋል፡፡ ከነዚህም ጥናቶች መካከል ሰይድ (1993)፣ አለማየሁ (1998)፣ ጌታቸው (2001) እና ኢሳያስ (2002) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አጥኚዎቹ በጥናታቸው እንዳሰፈሩት በአንደኛ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የጽህፈት ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ችግር ምክንያት የቋንቋ ትምህርት በሀገራችን የትምህርት መርሃ-ግብር ወይም በስርዓተ-ትምህርት ካለመካተት የመነጨ አይደለም፡፡ ችግሩ፣ ቋንቋው በትምህርትነት ቢቀርብም የክሂሉ አሰጣጥ የተዳከመና በተለይ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድረስ ትኩረት የተነፈገው እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህ ይህም ጥናት በኮሌጅ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በክሂሉ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ አማርኛ አፍፈትና ኢአፍፈት ተማሪዎች ለማጥናት ሲነሳ ቀደም ብሎ በቀረቡት አጥኝዎች የደረሱበት ድምዳሜ መነሻው ምንድን ነው? ለሚለውን ጥያቄ መልስ ይሰጣል ብሎ በማሰብ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ዓቢይ ዓላማ ስርም የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ተነድፈዋል፡፡

- አማርኛ አፍፈት እና ኢ-አፍፈት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን መመርመር፤
- አማርኛ አፍፈት እና ኢ-አፍፈት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በቋንቋው ህጎች /ስዋሰው/ የመጠቀም ችሎታቸው ምን ላይ እንደሚገኝ መገምገም፤
- አማርኛ አፍፈት እና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ ከፆታ አንፃር ያለውን ልዩነት መገምገም፤
- አማርኛ አፍፈት እና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ፤
- አጠቃላይ በጽህፈት ክሂል ላይ ያላቸውን ፍላጎትና ልምድ ማጥናት ናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝው ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሳው ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መፃፍ እማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ካለፈ ልምዱ በተግባር ያየው ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ መሻሻል በአማርኛ ቋንቋ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሰልጥነው የሚወጡት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው እና እነዚህ ሰልጣኞች ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ብሎ ከመመርመር በፊት እራሳቸው ሠልጣኞቹ ያላቸው የመጻፍ ብቃት ምን ያህል ነው? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጥያቄ በሁሉም ከፍተኛ ተቋማት ማጥናት ስለማይቻል አንድ ተቋም መምረጥ የግድ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አንዱ የሆነውን የጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ በአጥኝው ተመርጧል፡፡ ይህም ኮሌጅ የተመረጠበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በዲፕሎማ አሰልጥኖ የሚያስመርቅ በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ብቸኛ ተቋም መሆኑ፤ የተመረቁትም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ስለሚሰማሩ ለጽሕፈት ክሂል መሻሻልም ሆነ መዳከም የራሳቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ስለሚችሉ፤ አጥኝው በቀላሉ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚያስችለው፤ እንዲሁም በዚሁ ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል በሚያስተምርበት ጊዜ በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን ልምድና ያስተዋላቸውን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

በተጨማሪም ቀደም ሲል የተገለጹት አጥኚዎች ከደረሱበት ድምዳሜና ምሁራኑ ከሰጡት አስተያየት በመነሳት በአዲሱ ትምህርት ፖሊሲ አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻና እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተምረው ወደ ኮሌጅ ከገቡ ተማሪዎች ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ችግር በየትኞቹ ተማሪዎች ላይ ይሰተዋላል? በጽህፈት ችሎታቸውስ የትኞቹ ይሻላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የዚህ ጥናት አቅራቢ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማድረግ መወሰኑ ሌላው ምክንያት ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራንም ሆነ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ለሆኑ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የጽህፈት ክሂልን በተሻለ መንገድ

ለማስጨበጥ፣ በምንና እንዴት ይቅረብ የሚለውን ለመወሰን ለሚነሱ ጥያቄዎች መረጃ ይሰጣል፡፡ በትምህርት ክፍሉ ለሚገኙ ለሌሎች የክሂሎት ትምህርቶች መምህራን ለተማሪዎቻቸው ዘላቂ የክሂላቸውን መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡ ሌላው በዚህ ጥናት አጥኚው የአማርኛ ትምህርት ክፍል እጩ መምህራንን የጽህፈት ትምህርት በቀላሉ ለመከወንና ለዘላቂ የጽህፈት ክሂላቸው መዳበር መደረግ የሚገባቸውን በመጠቆም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል እምነት አለው፡፡

በተጨማሪም እጩ መምህራኑ የተሻሉ ፀሐፍት እንዲሆኑና ጥሩ የጽህፈት ክሂል እንዲይዙ ለሚያደረገው ጥረት በዚህ ጥናት የሚቀርበው መረጃ የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ተማሪዎቹ ተመርቀው ሲሄዱ እንዴት ጥሩ የጽሕፈት መምህር እደሚሆኑ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም በመስኩም ተመሳሳይ ጥናቶች እንዲደረጉ ያበረታታል፤ የመነሻ ሀሳብም ይሰጣል የሚል እምነት እንዳለው አጥኚው ይገልፃል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ተገቢነት ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ለጽህፈት ክሂል ያላቸውን ችሎታ በንጽጽር ማጥናት ስለሆነ ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን አይመለከትም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ለዚህ ጥናት የተሰጠው ጊዜ 6 ወር በመሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተጠኝዎች በፃፉት ድርሰትና ጽሑፍ መጠይቅ ላይ እንዲወሰን አድርጎታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃ ሰጪ ተማሪዎቹ የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት የማጠቃለያ ፈተና ላይ መሆናቸው ሌላው ለጥናቱ ውስንነት ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን ጥናቱ ከ 6 ወር በላይ ጊዜ ቢሰጠው በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ወይም አጥኚው ከተጠቀማቸው በተጨማሪ የቃል መጠይቅ፣ ምልከታ፣ የመምህራን ጽሑፍና ቃለ መጠይቅ፣ የትምህርቱን ሲለበስና ወዘተ. በደንብ ተፈትሾው ቢጠና ከዚህ የበለጠ ያደርገዋል የሚል እምነት አለው፡፡ በመሆኑም በተጠቆመው መሠረት በዚህ ዙሪያ ማጥናት ለሚፈልግ ተመራማሪ መንገዱን የሚጠቁም መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1 ንድፈ-ሀሳባዊ መሠረቶች

### 2.1.1 የጽህፈት ክሂል ምንነት

ጽህፈት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ክሂል በትምህርት አማካኝነት የሚቀሰምና ደረጃውን ጠብቆ ከሚፈፀም ተከታታይ ልምምድ የሚገኝ ችሎታ ነው፡፡ “ጽህፈት አካልንና አእምሮን በማቀናጀት በርካታ ባህሪያቱን በአንድ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው” በማለት Nunan (1989, 36) ያብራራሉ፡፡

ጽህፈት በትዕምርቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ ማስፈር መሆኑን የተለያዩ ምሁራን በጥናታቸው አብራርተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Byrne (1991, 1) "ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን ተጠቅሞ ሀሳብን በወረቀት ላይ የምናሰፍረበት ሂደት ነው" ብለዋል፡፡ ይህን ሀሳብ በማጠናከር Harmer (1991) እና Zamel (1985) ንግግር ድምፅ ከማመንጨት በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም ትዕምርቶችን አቀናብሮ የሚያቀርብ ነው በማለት በጥናታቸው አብራርተዋል፡፡

ከላይ ምሁራኑ ለማብራራት የፈለጉት የአንድ ቋንቋ ድምፆች ከሚወክሏቸው ምልክቶች ጋር እየተዛመዱ በወረቀት ላይ በማስፈር መልዕክት የሚተላለፍበት ክሂል መሆኑን ነው፡፡ ጽህፈት አንዱ የመግባቢያ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን መልዕክት ተቀባዩና መልዕክት ላኪው በወረቀትና በብዕር አማካኝነት መልዕክት ይለዋወጣሉ፡፡ እንዲሁም በድምጽ ምልክቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር ከሌላ አካል ጋር ለመግባባት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ከንግግር ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው፡፡

በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂል አካልና አዕምሮን በማስተባበር ድምፆችን በምልክቶች በመወከል ሀሳብን ለአንባቢ የምናቀርብበት ክሂል ነው፡፡ በጽሑፍ የሚቀርበው ሀሳብ ሊያግባባ የሚችለው የቋንቋውን ስርዓት የጠበቀ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ጽሑፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተደጋጋሚ በሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፣ ይዳብራል፣ ይበለጽጋል፣ እንዲሁም ጥሩ ፀሐፍት እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡

### 2.1.2 የጽህፈትን ክሂል ማስተማር የሚያስገኘው ጥቅም

የጽህፈት ትምህርት ከንባብ ትምህርት ጋር በጣም የተቆራኘ ግንኙነት አለው፡፡ ከነዚህ ሁለት ክሂሎች ቀዳሚ ተግባር ፊደል ከማስለየት ይጀምራል፡፡ የምናነበው በፊደል የተገነባ ነገር ነው፡፡ የምንጽፈው በፊደል አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህ የጽህፈት ትምህርት የሚያስገኘው ጥቅም በቋንቋው ውስጥ ያሉ ድምፆች የሚወክሏቸውን ምልክቶች ማስለየት ነው፡፡ ምንም እንኳ ፊደልን የማስለየት ተግባር የመጀመሪያው የጽህፈት ትምህርት አላማ ቢሆንም እንደ ተማሪዎቹ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ፍላጐት መሠረት በተለያዩ ደረጃዎች የጽህፈት ትምህርት አላማ ሊለያይ ይችላል፡፡

የጽህፈት ትምህርት አላማዎች ትግበራ በተማሪዎች እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ፍላጐት፣ ባላቸው ችሎታና ልምድ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ እነዚህ ነገሮች ግምት ውስጥ ካልገቡ ወደ ግብ ለመድረስ መሰናክል ሊሆኑ እንደሚችሉ Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡ በየክፍል ደረጃው የሚሰጠው የጽህፈት ትምህርት ዓላማና የሚያስገኘው ጥቅም የተለያየ ነው፡፡ በዝቅተኛ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች የፊደላትን ቅርጽ በመለየት ቃላትን መመስረት፣ የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማወቅ ሀሳባቸውን በተገቢ ቃላትና አረፍተ-ነገሮች መግለጽ የሚችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲያውቁ የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ የጽህፈት ትምህርት ከዚህም ሌላ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ላሉ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግና ስርዓት ጠብቀው ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ እንዲገልጹ ያስችላል፡፡ እንዲሁም ለማስተላለፍ የፈለጉትንም መልዕክት እነሱ እንዳሰቡትና እንደተረዱት በትክክል የሚያቀርቡለትን አካል ተገቢ ቃላት፣ አረፍተ-ነገሮችና የተዋጣለት አንቀጽ በመጠቀም /በማዋቀር/ በተገቢው መንገድ ለመግለጽ የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ በመሆኑም Heaton (1990) የጽህፈት ትምህርትን በመማር የሚከተሉትን ችሎታዎች ማዳበር እንደሚቻል ዘርዝረዋል፡፡

1. **የሰዋሰው ክሂሎች፡-** የቋንቋውን ህግና ስርዓት የጠበቁ አረፍተ-ነገሮችን መስርቶ ለአንባቢ ግልጽና ትክክለኛ መልዕክት ለማስተላለፍ የሚያስችል ብቃት እንዲኖር የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡
2. **የስልታዊነት ክሂሎች፡-** ስልታዊነት ማለት አንድ ፀሐፊ የሚከተለውን የአፃፃፍ ዘዴ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰማውን ውስጣዊ ስሜት ለመግለፅ የሚያስችሉ ቃላትን አመንጭቶ የመፃፍ ችሎታ እንዲኖረው የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

3. **የአፃፃፍ ስርዓት ክሂሎች፡-** የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት በመጠቀም በተገቢው ሁኔታ የመጠቀም ችሎታ እንዲኖር የጽህፈት ትምህርት ያግዛል፡፡
4. **የአጠቃቀም ክሂሎች፡-** ተገቢውን ቃላት ለተገቢው ቦታ መምረጥ ለሚቀረብለት አካል የማቅረብ ችሎታና ሀሳብን በትክክል በማቀናጀት የመፃፍ ብቃት እንዲኖር የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ይህም ማለት የቃላት አጠቃቀማችን የተደራሲያንን እድሜ፣ ፍላጎት፣ ባህል፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃና የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

የጽህፈት ትምህርት የተለያዩ የመማር ስልቶችንና ፍላጐቶችን ለማስገኘት እንደሚረዳ፤ የተለያዩ ክሂሎች በማቀናጀት መማር እንደሚያስችልና በመደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ፈተናዎችን ለማቅረብ እንደሚያገለግል ተብራርቷል፡፡ እንዲሁም የጽህፈት ትምህርት በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ድምፆችን የሚወክሉ የተለያዩ ምልክቶችን ከማሳየት አንስቶ ሀሳብን ተጠየቃዊና ቅደም ተከተላዊ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ የሚያስችል ብቃትን ያጐናጽፋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የጽህፈት ትምህርት የማስተማር ጥቅሞችን መሠረት በማድረግ ተጠኝ ተማሪዎች እምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለመመርመር ለጥናቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

## 2.1.3 የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦዎች

የጽህፈት ክሂል አላማው በኮሌጅ ደረጃ ተማሪዎች በጽህፈት ተግባቦት መገልገል እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን ክሂሎች ሁሉ አዳብረው ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ይህን ችሎታ ለማስገኘት በሚደረግ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ በርካታ መሰናክሎች ይኖራሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ Nunan (1989), Hedge (1988), Norrish (1990) እና Richards (1990) ገልጸዋል፡፡

### 2.1.3.1 የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን

የጽህፈት ክሂል በቀላሉ የሚጨበጥ ክሂል አይደለም፡፡ ክሂሉ ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ክሂል ነው፡፡ በተለይ ደግሞ አስቸጋሪነቱን የሚያጐላው እንደማዳመጥና መናገር በልምድ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ የጽህፈት ስራ ሀሳብን ከማደራጀት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡ አዕምሯዊ እና አካላዊ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሀሳብን በጽሑፍ ለማስፈር ጊዜ ይወስዳል፡፡

እነዚህ ሁሉ ባህሪያቱ ውስብስብነቱንና አስቸጋሪቱን ያሳያሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ወስዶ ተጽፎም በመጨረሻ ውጤቱ የታሰበውን ያህል የተፈለገውን መልዕክት ላያስተላለፍና ላያረካ ይችላል፡፡ የጽህፈት ክሂል ምልክቶችን በወረቀት ላይ ከማስፈር ያለፈ ነገር ነው፡፡ አንዱ የተዋጣለት ጽሑፍ አጠናቅሮ ለማቅረብ ብዙ ነገሮችን ማወቅ ይጠይቃል፡፡ ከነዚህ ችሎታዎች መካከል የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሀሳብና መረጃዎችን አቀናጅቶ አጠናቅሮ ማቅረብ፣
2. ከአሻሚነት ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ፣
3. ለአጽንኦት ሲባል ውስብስብ ያሉ ሰዋስዋዊ ሰርዓቶችን አለመጠቀም፣
4. ጥንቃቄ የተሞላ የቃላት ምርጫና አጠቃቀምን መከተል፣
5. ተገቢውን የሰዋስው አጠቃቀም መከተልና የአረፍተነገር መጠን መወሰንን ማወቅ፡፡

ከላይ የቀረቡት የጽህፈትን ውስብስብነት የሚያሳዩት ነጥቦችና ጽህፈትን አጠናቅሮ ለማቅረብ የሚረዱት ነጥቦች ተጠኝ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ከተነሱት አምስት ነጥቦች የትኛው ላይ የተሻለ ትኩረት እንዳላቸው ለማወቅ አስችሏል፡፡

## 2.1.3.2 ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊ እና አዕምሯዊ ባህሪያት

በጽህፈት ትምህርት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ተላውጦዎች መካከል ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊና ስነአዕምሯዊ ሁኔታዎች እንደሆኑ Byrne (1991), Richards (1990) እና Norrish (1990) ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ቀጥለን የተወሰኑትን በዝርዝር እንመልከት፡፡

**ሀ. ስነልቦናዊ ባህሪ፡-** ጽህፈት የማፍለቅ ተግባር የሚከናወንበት ክሂል እንደመሆኑ መጠን አንባቢን እያሰቡ መፃፍ የማይቀር ነው፡፡ ፀሐፊውም መልዕክቱን ለአንባቢ ግልጽና ሳቢ በሆነ መንገድ ለማድረስ ሲል ከወዲሁ በሀሳብና በጭንቀት የሚሞላበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም የጽህፈት ክሂልን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በንግግር ጊዜ ግን ተናጋሪው ወዲያውኑ ከአድማጩ ግብረ-መልስ ስለሚያገኝ መልዕክቱን ማስተካከል ይችላል፡፡ በጽህፈት ጊዜ ግን የአንባቢው ግብረ-መልስ የዘገየ ነው በማለት Byrne (1991) ያብራራሉ፡፡

በመሆኑም በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች አንደኛው በተግባር ከልምድ እንደተገነዘብነው መፃፍን የሚፈሩት ከላይ እንደተገለጸው የምጽፈው ድርሰት በትክክል ተነባቢነት ይኖረው ይሆን? ወይም የት ላይ እሳሳት ይሆን? በማለት ከራሳቸው ጋር ስለሚሟገቱ ስነልቦናዊ ችግር

ሲገጥማቸው እናያለን፡፡ በዚህም ጥናት በተለይ በአማርኛ አፍፌት ተማሪዎች ላይ ስነልቦናዊ ችግር ተስተውሏል፡፡ ስለዚህ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት እንዳለውና በጥናቱም የተረጋገጠ ነው፡፡

**ለ. ስነልሳናዊ ባህሪ፡-** በጽህፈት አማካኝነት ሀሳብን በሚገባ ለማስተላለፍም ሆነ በታላሚው ቋንቋ አማካኝነት ተጽፎ ወይም ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን መልዕክት ለመረዳት የቋንቋውን ውስጣዊ ባህሪ ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ በንግግር ሂደት ውስጥ ጠቃሚነት የሌላቸውንና የምንተዋቸውን ሁሉ ደግመን በማለት ወይም እንደገና አስተካክለን ለመናገር እድል ስላለን ልናስተካክለው እንችላለን፡፡ ይህ ሁኔታ በጽህፈት ጊዜ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም ስንጽፍ በጣም ተጠንቅቀን፣ አስበንና ጊዜ ወስደን እያንዳንዱን ቅንጣት አስተካክለን ማቅረብ ይኖርብናል በማለት Byrne (1991) እና Norrish (1990) ያስረዳሉ፡፡ ይህም ከላይ እንደተገለጸው የጥናቱ ተማሪዎች በየፋት ድርሰት አማርኛ አፍፌትና ኢ-አፍፌት ከሆኑት የትኞቹ በጥንቃቄ እንደፃፉ ለመለየት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

**ሐ. ስነአዕምሯዊ ባህሪ፡-** ጽህፈት በልምድ ሳይሆን በትምህርት ሂደት የሚገኝና የአዕምሮን ውስጣዊ ረቂቅ ተግባር የሚጠይቅ ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ እንዲሁም እንደየደረጃችን ፈተናን ለማለፍ አልያም ለክሂልነት ብቻ የምንማረው ጥበብ አይደለም፡፡ ይልቁንም ትምህርቱ ሌሎች ክሂሎችን ለመማርና ተጨማሪ እውቀቶች ለመቅሰሚያነት ያገለግላል፡፡ የጽህፈት ክሂል እጅን፣ ዓይንና አዕምሮን በማጣመር ተግባቦትን ለማፋጠንና ገጠመኞችን ለማካፈል የሚያገለግል ስለሆነ ውስብስብ የሆነ አዕምሮታዊ ባህሪ አለው፡፡ ክሂሉንም ለማዳበር ሰፊ ጊዜና በቂ ልምምድ የሚጠይቅ ጊዜ ወሳጅ ክሂል ነው፡፡ ስለዚህ አዕምሮን በማሰራት ሀሳብን በጽሑፍ መግለጽ አለመቻል ለጽህፈት ትምህርት አስቸጋሪነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡

በአጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት ክሂልን ለማዳበር ሰፊ ጊዜና በቂ ልምምድ ማድረግን የሚጠይቅ ሲሆን ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የተለያዩ ጉዳዮች (ተላውጦዎች) ጎልተው ይታያሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ክሂሉን ለማስጨበጥ ሲያቅዱ ትኩረት በማድረግ የተማሪዎቹን የስነልሳን ሁኔታ በቋንቋው ያላቸውን የዕውቀት ደረጃና የአዕምሮ ብስለታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክሂሉ መዳበር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም “ጽህፈት ሀሳብን ከአዕምሮ አመንጭቶ በወረቀት ላይ አስተካክሎ ማስፈር ከባድና አዕምሮን ሊፈትን ይችላል” በማለት Byrne (1991, 4) ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.4 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

በአሁኑ ጊዜ እየተሰራባቸው ያሉት የጽህፈት ክሂል አቀራረብን ውጤት ተኮር አቀራረብ እና ሂደታዊ አቀራረብ ናቸው በማለት Nunan (1989) እና Richards (1990) በሁለት እንደሚመደቡ ያስረዳሉ፡፡

#### 2.1.4.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ

ውጤት ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ ትኩረቱ ከጽህፈት ሂደት ይልቅ ተማሪዎች በሚያፈልቁት የመጨረሻ ውጤት ላይ ነው፡፡ በዚህ አመለካከት የተማሪዎች የመፃፍ ብቃት ከፍ ሲል ውስብስብ የጽህፈት ተግባራትን የመቆጣጠር ችሎታን ያዳብራሉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ብዙ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ፡፡ የአረፍተ-ነገርና የአንቀጽ አደረጃጀት ቅንብር ይካናሉ በማለት Nunan (1989) እና Richards (1990) ይገልፃሉ፡፡

ይህ አቀራረብ የጽህፈትን ምንነት የሚለካው የሰዋስው ህግጋትን ተክተሎ በጽህፈት ከመተግበር አንፃር ሲሆን አይነተኛ ትኩረቱም በስተመጨረሻ ተጠናቆ የሚቀርበው ሥራ ላይ እንጂ ጽሑፍ እንዴት እንደሚዘጋጅ በሚፈፀመው ሂደት ላይ አይደለም፡፡ አቀራረቡ በአንድ በኩል ተማሪዎች ልዩ ልዩ የጽህፈት ሥራዎችን እንዲያዘጋጁ የሚረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ስህተት እንዳይሰሩ የሚከለክል እንደሆነ Richards (1990) ያስረዳሉ፡፡ ለቅርጽ ከፍተኛውን ትኩረት የሚሰጠው በዚህ አቀራረብ ብዙውን ጊዜ በድርሰት ርዕስ መምህሩ ተጽእኖ የሚያደርግ ሲሆን አረፍተ-ነገር ምስረታ፣ ባዶ ቦታ መሙላት፣ አረፍተ-ነገር ማስፋፋት፣ አንቀጽ ማዳበርና ወዘተ. የተለመዱ ተግባሮች ናቸው፡፡ በውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ጽህፈትን ሲማሩ ሦስት ደረጃዎች እንዳሉት Pincas (1982), Kamrul እና Mohd. (2010) ያስረዳሉ፡፡

1. **የትውውቅ ደረጃ፡-** ተማሪዎች ወደ ዋናው የጽህፈት ሥራ ከመግባታቸው በፊት በመምህራን የሚቀርብላቸውን ሞዴል ጽሑፍ በማንበብ ለመፃፍ ራሳቸውን የሚያዘጋጁበትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ደረጃ ነው፡፡ በመሆኑም Pincas (1982, 14) "ለተማሪዎች በመምህራን ተመርጦ የሚቀርበላቸው ሞዴል ጽሑፍ ሊያነሳሳቸው የሚችል መሆን አለበት፡፡ ከዚህም ሌላ እድሜያቸውን፣ የክፍል ደረጃቸውን፣ ባህላቸውንና ፆታቸውን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል" በማለት ያስረዳሉ፡፡

2. **የልምምድ ደረጃ፡-** የልምምድ ደረጃ የተማሪዎች የተለያዩ ሞዴል ጽሑፎች ጋር ከተዋወቁ በኋላ በራሳቸው ተነሳሽነት የራሳቸውን ሀሳብ እያፈለቁ መፃፍን እንዲለማመዱ የሚደረግበት

ደረጃ ነው፡፡ ይህንም Pincas (1982, 18) "ተማሪዎች በልምምድ ደረጃ ውስን ጽህፈትን ተለማምደው ቀስ በቀስ ወደ መሪ የጽህፈት ክንውን ደረጃ የሚሸጋገሩበት ነው" በማለት ያጠናክሩታል፡፡

**3. የውጤት ደረጃ፡-** በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተለማመዷቸውን የጽህፈት ስራዎች ወደ ውጤት የሚቀይሩበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎች ያለማንም እገዛ የሚሰጣቸውን የጽህፈት ትምህርት ደስ እንዳላቸው በነፃነት ያከናውናሉ፡፡ የመምህራን ሚና አነስተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ሀሳባቸውን እያፈለቁ በነፃነት የሚጽፉበት፣ አቅማቸውን የሚያጐለብቱበት ነው፡፡ እንዲሁም ሀሳባቸውን በወረቀት ላይ እንዲያሰፍሩ ይፈለጋል፡፡ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነቱ፣ የአንቀጽ አደረጃጀቱ፣ የቃላት አመራረጡ በመጨረሻ ላይ የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው በማለት Raimes (1983) እና Hedge (1988) ያስረዳሉ፡፡

## 2.1.4.2 ሂደታዊ አቀራረብ

ተመራማሪዎች ውጤት ተኮር አቅራረብ ጽህፈትን በማስተማር ረገድ ድክመት እንዳለው በቅርብ አመታት አመልክተዋል፡፡ ውጤት ተኮር አቀራረብ አትኩሮቱ ክሂሉን ከማሳደግ ይልቅ መድረስ ላይ ነው፡፡ ተማሪው በሂደት የተለያዩ ደረጃዎችን እያለፈ እንዲመጣ ሳይሆን የታሰበው ግብ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም የጥሩ ፀሐፊዎች ሂደታዊ አቀራረብ ምርጫቸው አድርገዋል፡፡ ሂደታዊ አቀራረብ አይነተኛ መገለጫው ፀሐፊው በመፃፍ ሂደት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በመግለጽ ላይ ማተኮር ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ በትክክለኝነቱ ምትክ የፀሐፊው የአፃፃፍ ሂደት ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል፡፡ የዚህ ፈለግ አራማጆች ትኩረት የሚያደርጉት በመጨረሻ ተጠናቆ በሚቀርበው የጽህፈት ውጤት ሳይሆን ወደ እዚያ ለመድረስ የሚያስችለው ሂደት ላይ ነው፡፡ ፀሐፊውም አዘውትሮ እራሱን የሚጠይቀው ስለጽሑፉ አላማና ስለአንባቢያን ሳይሆን ጽሑፍን እንዴት ልጀምረው እንዴትስ ሀሳቤን አቀናጅቼ ልፃፈው የሚል ጉዳይ ላይ ነው በማለት Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡ በዚህ የጽህፈት አቀራረብ ተማሪዎች ድርሰታቸውን የሚጽፉት በውጤታዊ አቀራረብ እንደሚዘወተረው በመምህሩ ተወስኖ በሚሰጣቸው ርዕስ አይደለም፡፡ እራሳቸው የሚሰማቸውን ርዕስ ይመርጣሉ፡፡

የጽሑፋቸውን ረቂቅ ለመምህራን ለጓደኞቻቸው ያሳያሉ፡፡ የሚያገኙትም ምላሽ ይበልጥ እንዲያስቡበት ይገፋፋቸዋል፡፡ በጽህፈት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉ፡፡ የጽህፈት ስራ የሚያከናውነው ሰው ሊያከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች ለመፃፍ መነሳት ሀሳቦችን ማገናኘት፣

ሀሳብን በቢጋር መልክ ማዘጋጀት፣ ማስታወሻ መውሰድና የመጀመሪያውን ረቂቅ መፃፍ፣ መከለስ፣ እንደገና ማቀድ፣ ደግሞ ማርቀቅ በመጨረሻም ለህትመት ማዘጋጀት በተባሉት ክዋኔዎች ውስጥ እንደሚያልፍ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች ቅድመ ጽህፈት፣ የጽህፈት ጊዜ እና ድህረ ጽህፈት በሚባሉ ዋና ዋና የጽህፈት እርከኖች እንደሚከፈል Richards (1990) እና Hedge (1988) ያብራራሉ፡፡

## 2.1.4.2.1 ቅድመ ጽህፈት

ፀሐፊዎች ሀሳብን የሚሰበስቡበት፣ አንባቢን የሚያስቡበት፣ አበይት ነጥቦችን የሚያቀርቡበት፣ ጊዜያዊ እቅዳቸውን የሚነድፉበት በአጠቃላይ ወደ ዋናው የጽህፈት ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ውስጥ ቢጋር ማውጣት ወሳኙ ጉዳይ ነው፡፡ ቢጋር በታላሚዉ ጽሑፍ ውስጥ ምን ምን ነጥቦች እንደሚካተቱ ጠቅለል ጠቅለል እያደረጉ በስርዓት ማስፈር ነው፡፡ ይህ ቢጋር ከመጨረሻው ጽሑፍ በኋላ ሊታረሙ እንደውም ሊቀር ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያት ሁለት አይነት የቢጋር አወጣጦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አንድ ጽሑፍ ከመፃፍ በፊትና የሁለተኛው ጽሑፍ ከተጠናቃቀ በኋላ የሚወጡ ቢጋሮች ናቸው፡፡ በማፍለቅ ጊዜ የተሰበሰቡ ሀሳቦች ይመረጡና በአጭር በአጭሩ በቢጋር ላይ ተደራጅተው ከሰፈሩ በኋላ ሀሳቡ እንዳይደባለቅበት በወገን በወገን ለመለየት፣ የተሰበሰበው ሀሳብ ያለቦታው እንዳይገባና የአስተሳሰብ ሂደቱን እንዳይገድብበት ይረዳዋል በማለት በድሉ (2007) እና Richards (1990) ያብራራሉ፡፡

## 2.1.4.2.2 የጽህፈት ጊዜ

ሁለተኛ የጽህፈት ደረጃ በቅድመ ጽህፈት የተመረጠውን ሀሳበ መልክ በማስያዝ በወረቀት የሚሰፍርበት ነው፡፡ ረቂቁን ከማርቀቅ ይነሳል፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት ቅርጾችንም ይጠቁማል፡፡ እነዚህም ቅርፆች መግቢያ፣ ዋና አካል መደምደሚያ ናቸው፡፡ ይህ የሀሳብ አደረጃጀት ቅርጽ በአብዛኛው በአጭርና በረጅም የጽሑፍ አይነት ያገለግላል፡፡

**ሀ. መግቢያ፡-** አንባቢን ከመጀመሪያው ለንባብ የሚያነሳሳ መሆን ይገባዋል፡፡ በእርግጥ መግቢያው የማንበብ ፍላጎትን የሚያነሳሳ ሳቢ ሊሆን ይገባዋል፡፡

**ለ. ዋና አካል፡-** የዋና አካል ተግባሩ በመግቢያው የተጠቀሱትን ነጥቦች ማጠናከር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- መዘርዝር፣ ምክንያት፣ ማብራሪያ፣ ምሳሌ መስጠትና ወዘተ. ነጥቦቹን የበለጠ ግልጽ

እንዲሆኑና እንዲታወቁ ማድረግ ነው፡፡ በምሳሌው ስር የተዘረዘሩት ያለ መግቢያ በዋናው አካል ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ዋና አካል በአጭርም ሆነ በረጅም ጽሑፍ የማይቀር ነው፡

**ሐ. መደምደሚያ፡-** ጽሑፉ ማለቁን የምንገልጽበት ክፍል ነው፡፡ አንድ ፀሐፊ መደምደሚያ ሲጽፍ የተለያ ቴክኒኮችን ይጠቀማል፡፡ አመልካች ቃላት በመጠቀም የመጨረሻዎቹን አረፍተ-ነገሮች አካሄድ በመለወጥ ምስያ በመፍጠር እና ወደ መግቢያዉ በመመስ መደምደም ይቻላል፡፡

## 2.1.4.2.3 ድህረ ጽህፈት

በዚህ ደረጃ ጠቅላላ የክለሳ ንባብ የሚደረግበት በመሆኑ ተደራሲያኑ ያለምንም ችግር ጽሑፉን አንብበው ሀሳቡን እንዲያደንቁ ለማድረግ የሚስተካከል ነገር ካለ የሚስተካክልበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ፀሐፊው ለአንባቢው ያስቸግራሉ የሚላቸውን ቃላት በመምረጥ፣ የአረፍተ-ነገሮችን አደረጃጀት በማስተካከል አስተዋጽኦ መስጠት የሚፈለገውን ሀሳብ በተገቢው ቦታ መቅረብ አለመቅረቡን የሚመለከትበት ነው፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሁለት የጽህፈት ክሂል አቀራረቦች ወይም ከውጤት ተኮር አቀራረብና ከሂደታዊ አቀራረብ አጥኚው ይዞት ከተነሳው ምርምርና ከተጠኝዎቹ የጽህፈት ክሂል ደረጃ አንፃር ተመራጭ የሚያደርገው ሂደታዊ አቀራረብን ነው፡፡ ምክንያቱም ውጤት ተኮር የመምህሩ ሚና ይበዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሚጽፉት ድርሰት አብዛኛውን ጊዜ ርዕስ የሚመርጠው መምህሩ መሆኑ እንዲሁም ተማሪዎቹ ከስህተት እንዲማሩ አለመፍቀዱና የመጨረሻው ውጤት ላይ ማተኮሩ አሁን ካለንበት የመማር ማስተማር ዘዴ ጋር ተጣጥሞ አይሄድም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከላይ በተገለፀው መልኩ ተማሪዎችን የምናስጨንቃቸው ከሆነ የጽህፈት ክሂልን ከነአካቴው እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል፡፡

በመሆኑም የጽህፈት ክሂል ለአፍፈትም ይሁን ለኢ-አፍፈት ተመራጭ የሚሆነው ሂደታዊ አቀራረብ ነው፡፡ ምህንያቱም ለመምህሩ ሳይሆን ለተማሪዎቹ ነፃነት ስለሚሰጣቸውና ጽህፈትን በሂደት እንዲያዳብሩ ስለሚያደርጋቸው፤ ድርሰትም ለመፃፍ ርዕስ እራሳቸው እንዲመርጡ እድሉን ስለሚሰጣቸው፤ የመምህሩ ጫና ስለማይበዛባቸው እንዲሁም ከስህተታቸው እንዲማሩ አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ፤ የጽህፈት ክሂል ፍላጎታቸው ከፍ ስለሚል በሂደት ከአንድ ደረጃ ወደ አንድ ደረጃ በሄዱ ቁጥር የተሻሉ ፀሐፍት እንዲፈጠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናትም ዋና አላማ ተጠኝዎቹ ያለባቸውን የጽህፈት ችግር በሂደት የሚቀርፉበትን መንገድ

መጠቆምና ጥሩ ፀሐፍት እንዲሆኑ መንገዱን ማመላከት ስለሆነ ሂደታዊ አቀራረብ ከዚህ ጥናት ጋር ስለሚሄድ በአጥኚው ተመራጭ ነው፡፡

## 2.1.5 የጽህፈት ክሂል መልመጃ አይነቶች

ጽህፈትን በማስተማር ሂደት የጽህፈት ክሂል መልመጃ ተማሪዎችን የሚያግባቡ ወይም መልዕክት ያለው ጽሑፍ እንዲዘጋጁ የሚያበረታቱ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ስለሆነም የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሲዘጋጁ ከዚህ ቀጥለን የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ብናተኩር የተሻለ እንደሚሆን Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡

1. የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ተግባራዊና ጠቃሚ በሆኑ የጽህፈት አይነቶች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል፡፡
2. የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች የሚያተኩሩበት ልምምድ ተግባቦታዊ ወይም አገልግሎታዊ መሆን አለበት፡፡
3. የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሰዋስውና ቃላትን ለማስተማር ከመርዳታቸው ጐን ለጐን ሌሎች ክሂሎችንም ለማሳደግ የሚረዱ መሆን አለባቸው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ተማሪው ክሂሉን በመጠቀም መልዕክት ማስተላለፍና መግባባት እንዲችል በተግባር ሊተረጐሙ የማይችሉና በደረጃው ተማሪው በማህበረሰቡ ውስጥ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ሀሳቦችን ያልያዙ ሆን ብለው የተዘጋጁ መልመጃዎት መሆን የለባቸውም፡፡ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሰዋስውና ቃላት ከማስተማር በላይ ተማሪው እንዴት መፃፍና ምን አይነት የአፃፃፍ ዘዴዎችን መከተል እንዳለበት የሚያስረዱ መሆን አለባቸው፡፡ በመሆኑም የጽህፈት ክሂል መልመጃ አይነቶች ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ፣ ጠቋሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃ እና ልቅ የጽህፈት ክሂል መልመጃ በማለት በሦስት እንደሚከፈሉ Pincas (1982) እና Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.5.1 ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ

ይህ የጽህፈት ክሂል መልመጃ ትኩረት የሚሰጠው ለትክክለኛነት ነው፡፡ ተማሪው እንዲሰራ የሚደረገው እጅግ ውስን የሆነ ነገር ነው፡፡ ከራሱ አፍልቆ የሚጨምረውና በራሱ ፍላጐት የሚከተለው የአሰራር መንገድ አይኖርም፡፡ በመሆኑም Raimes (1983, 95) "ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ በአብዛኛው የጽሑፍ ቅርጽና ይዘት ለተማሪው ተሰጥቶት የሚሰራው መልመጃ ነው" በማለት ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ያጠናክሩታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Pincas (1982)

ተማሪዎች ትክክለኛ የሆነ የጽሁፈት ስራ ውጤት ለማቅረብ መመሪያ ጠብቀው የሚጽፉበት፣ የሚሰሩት ባዶ ቦታ በመሙላት የሚጽፉበት የጽሁፈት ክሂል መልመጃ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ የሚሰሩት ባዶ ቦታ በመሙላት የተለያዩ አረፍተ-ነገሮችን በማያያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎት ውስን ተግባር እንዲያከናውኑ የሚከተሉት ናሙና በመኖሩ ስህተት የመሰራት እድላቸው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ውስን የጽሁፈት ክሂል መልመጃ በየትኛውም ደረጃ ጽሁፈትን የሚማሩ ተማሪዎች ከመጀመሪያ ወደ ሌላ የጽሁፈት ክሂል መልመጃ ከመሄዳቸው በፊት ልምምድ ሊያደርጉበት የሚገባ የመልመጃ አይነት ነው፡፡

### 2.1.5.2 ጠቋሚ የጽሁፈት ክሂል መልመጃ

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች እንዲለማመዱና እንዲጽፉ የሚፈለገው ጽሑፍ ፍንጭ ሊሰጣቸው የሚችልና እንደመመሪያ ሊገለግላቸው የሚችሉ የናሙና ጽሑፍ ይቀርብላቸዋል፡፡ ተማሪዎች ጠቋሚ የጽሁፈት ክሂል መልመጀዎች በሚሰሩበት ጊዜ ከውስን የጽሁፈት ክሂል መልመጃ በተሻለ መልኩ የራሳቸውን ሀሳብ የመጨመር ነፃነት አላቸው፡፡ የሚጽፉትና በመጨረሻ የሚገኘው ውጤት ተመሳሳይነት የሚኖረው ነው በማለት Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Raimes (1983) ጠቋሚ የጽሁፈት ክሂል መልመጃ በውስንና በልቅ የጽሁፈት ክሂል መልመጃዎች መካከል ያለ ድልድይ ነው፡፡ መልመጃውን ተማሪዎት በሚለማመዱበት ጊዜ የሚከተሉትን ናሙና አስፋፍተው ሊጽፉ የሚችሉት አስተዋጽኦው የተፃፈና ግማሹን እንዴት እንደሚጨርሱት ፍንጭ የሚሰጥ ጽሑፍ ወይም ልክ እንደሚነበብ ጽሑፍ አዲስ ሀሳብ የያዘ ስዕል በማቅረብ ድጋፍ በመስጠት እንዲጽፍ የሚያደረግ የጽሁፈት ክሂል መልመጃ አይነት ነው፡፡ ተማሪዎት የተጀመረ ጽሑፍ ተሰጥቷቸው እንዲጨርሱ በተጠየቁ ጊዜ ጽሑፉን መጨረስ ሲለማመዱ ከራሳቸው ያፈለቁትን ሀሳብ ከተሰጠው ጽሑፍ ጋር እንዲስማማ አድርገው መጨረስ አለባቸው፡፡ የጽሑፉን ሀሳብ ሳያዛቡ በቅደም ተከተል በራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው ለመፃፍ ዝግጅት የሚያደርጉበት የጽሁፈት ክሂል እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

### 2.1.5.3 ልቅ የጽሁፈት ክሂል መልመጃ

ልቅ የጽሁፈት ክሂል መልመጃ ከሌሎች የጽሁፈት መልመጃዎች የሚለይበት ተማሪዎች እራሳቸው አፍልቀው እንዲጽፉ ነፃነት የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ይህ የመልመጃ አይነት ባዶ ቦታዎች እንዲሞሉ፣ የተጀመሩ አረፍተ-ነገሮችን እንዲጨርሱ፣ የአንድን ጽሑፍ የተወሰነ ክፍል እንዲጨርሱ ሳይሆን በታዘዙት መሠረት ከራሳቸው አፍልቀው በራሳቸው መንገድ አቀናጅተው

ስርዓት በማስያዝ የጽሑፍ ስራ እንዲያቀርቡ የሚያደርግ የመልመጃ አይነት ነው በማለት Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.6 ለመፃፍ የሚያነሳሱ ተግባራት

ተማሪዎች የጽህፈት ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማገዝ የተለያዩ መልመጃዎች ተሰጥቶ ተከታታይ ልምምድ እንዲተገብሩ ማድረግ ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡ በዚህ ልምምድ ሂደትም ተማሪዎች አዳዲስ ልምዶችን ያዳብራሉ፡፡ የጽህፈት ችሎታቸውንም ቀስ በቀስ ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግራሉ፡፡ ተማሪዎች እንደ ክፍል ደረጃቸው የጽህፈት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚረዱ ሦስት የጽህፈት መለማመጃ ተግባራት እንዳሉ Celce-*Murcia* (2001) ያስረዳሉ፡፡ ተግባራቱንም ቀጥለን በዝርዝር እንመልከት፡፡

#### 2.1.6.1 ተግባራዊ የጽህፈት መለማመጃዎች

ተግባራዊ የጽህፈት መለማመጃዎች ቅደም ተከተላዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ ልምምድና ሂደትም በማለማመጃነት ሊያገለግሉ የሚችሉት አጭር መልዕክቶች፣ ቀላል ትዕዛዞች የክፍል ስራዎች ሲሆኑ እድገት እያገኙ ሲሄዱ የማስታወሻ፣ የግብዣ፣ የመልዕክት፣ የሰላምታና የምስጋና ጽሑፎችን እንዲጽፉ ያደርጋል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን የመልመጃ ስልቶች በመጠቀም ተማሪዎች የተለየዩ ጽሑፎችን በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ እንዲጽፉ በማድረግ የተማሪዎችን ፍላጐት ማነሳሳት ይቻላል በማለት Celce-*Murcia* (2001) ያብራራሉ::

#### 2.1.6.2 የስሜት መግለጫ ጽሑፎች

ስሜት መግለጫ ጽሑፎች በማለት ከተጠቀሱት ውስጥ ለጓደኛ ደብዳቤ መፃፍ፣ ስለዕለት ውሎ መመዝገብን፣ ስለሌሎች ያለንን አመለካከት ወዘተ. መፃፍን ያካትታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አይነቱ ጽሑፍ የተማሪዎችን ውስጣዊ ፍላጐት የሚስቡ በመሆናቸው በከፍተኛ የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች እንጂ በዝቅተኛ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች እንደማይሆን Celce-*Murcia* (2001) ይጠቁማሉ፡፡

#### 2.1.6.3 ትምህርት ቤት ተኮር የጽህፈት መለማመጃዎች

ጽህፈትን ሕይወታዊ እንዲሆን የሚያደርገው ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ላይ ተመስርተው ሲጽፉ ነው፡፡ ትምህርት ቤታቸው በተማሪዎች አቅራቢያ ስለሚገኝ በትምህርት ቤት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለመገንዘብ ቅርበቱ አስተዋጽኦ ስላለው የሚሰማቸውና

የሚሰጣቸውን ሀሳብ ለማደራጀት ሁኔታው ምቹ ይሆንላቸዋል በማለት ትምህርት ቤት ተኮር ጽሑፎች የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማለማመድ ያለውን ፋይዳ Celce-*Murcia* (2001) ያስገነዝባሉ፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ለጽህፈት የሚያነሳሱ ተግባራት Raimes (1983) እና Ur (1996) በሚከተለው መልኩ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ተማሪዎችን እንዲጽፉ የሚያነሳሳቸው ጉዳዮች፡-

- ተማሪዎች መጽሐፍ እንዲያነቡና ስለአነበቡት መጽሐፍ እንዲጽፉ ማድረግ
- አንድ ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ ያነበቡትን በራሳቸው አባባል ጨምቀው አሳጥረው እንዲጽፉ ማድረግ
- አንድ ስእል በማሳየት ከስዕሉ የተገነዘቡትንና የተሰማቸውን እንዲጽፉ ማድረግ
- ግላዊ የሕይወት ተሞክሯቸውን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍሉ ውጭ እንዲጽፉ ማድረግ
- ስለጓደኞቻቸው ወይም ስለሚያውቁት ሌላ ሰው እንዲጽፉ ማድረግ
- የተለያዩ ደብዳቤዎችን እንዲጽፉ ማድረግ፣ ለምሳሌ፣ የሰላምታ ደብዳቤ፣ የግል ደብዳቤ፣ ልዩ ልዩ የጥሪ ደብዳቤዎች ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎች እንዲጽፉ ማድረግ
- ተማሪዎች በሬዲዮና ቴሌቪዥን ያደመጡትን ዜና በራሳቸው የዜና ዘገባ እንዲያዘጋጁ ማድረግ
- ትምህርት ቤታቸውን በተመለከተ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ
- የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉ በመጋበዝ ስለተመለከቱትና ስለተገነዘቡት ነገር እንዲጽፉ ማድረግ
- የተጀመሩ የተለያዩ ጽሑፎችን በመስጠት ጅምሩን አሟልተው እንዲጽፉ ማድረግ በማለት የዘረዘሩ ሲሆን ትልቅ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ነገር ፍላጎት ለጽህፈት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.1.7 የውጤት አሰጣጥ መስፈርትና የማረሚያ ኮድ

እስከ አሁን ድረስ አንድ ወጥ የሆነ የማረሚያ መስፈርት የለም፡፡ መምህራን የራሳቸውን የማረሚያ መስፈርትና ማረሚያ ኮድ በመጠቀም የተማሪዎችን ጽህፈት ማረም ይችላሉ፡፡ ይህንም ሀሳብ Hedge (1988, 148) "አንድ ወጥ የሆነ የውጤት አሰጣጥ መስፈርትና የማረሚያ ኮድ የለም" በማለት ያጠናክሩታል፡፡ በመሆኑም መምህራን ከተማሪዎች እድሜ፣

የክፍል ደረጃና ከጽሑፉ አላማ አንፃር የራሳቸውን የጽሑፍ መቆጣጠሪያ ዝርዝርና የውጤት ማረሚያ መስፈርት ከሌላቸው አንድ የማረሚያ መስፈርት ብቻ የበለጠ አመቺና ሁልጊዜ የሚሰራበት ተደርጐ መውሰድ የለበትም፡፡ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ደረጃና ፍላጐት በመረዳት የራሳቸውን የማረሚያ መስፈርት መከተል ወይም ካሉት የማረሚያ መስፈርቶችና ኮዶች የሚያመቻቸውን መርጠው ማከናወን ይችላሉ፡፡

## 2.1.8 የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ነጥቦች

አንድ ጽሑፍ የተዋጣለት ነው የሚባለው ከፊደል ቅርጽ አጣጣል አንስቶ የቃላት መረጣ፣ የሰዋስው አጠቃቀም፣ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና የአንቀጽ አወቃቀር ያሉትን ችሎታዎች በአግባቡ ሲያካትት ነው፡፡ የጽህፈት ክሂል የሰዋስው አገባብን ጠብቆ ቃላትን በአረፍተ-ነገሮች አቀናጅቶ የማቅረብ ችሎታ መኖር ብቻ ሳይሆን ሀሳብን በተገቢ መንገድ በማፍለቅ ተጠዪቃዊ በሆነ መንገድ የማደራጀትንም ችሎታ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም Pincas (1982, 32) "የማግባባት ብቃቱ፣ ተጠይቃዊ አደረጃጀት፣ በቅርጽና በአቀራረቡ፣ በሰዋስው ቅንብር ደረጃውና በእጅ ጽህፈት፣ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም መስፈርቶች የጽህፈት ክሂል ሊመዘንና ሊገመገም ይችላል" በማለት ሀሳቡን ያጠናክሩታል፡፡

በመሆኑም ምሁሩ ከላይ የገለጹትን መስፈርት አጥኚው ተጠኚዎች የፃፉትን ድርሰት ከላይ በተቀመጡት የጽህፈት ችሎት መመዘኛ ነጥቦች አንፃር በመገምገም እርማት በማካሄድ ውጤት ለመስጠት ስሚያስችለው ተቀባይነት ያለው፣ የሚስማማበትና ለጥናቱ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ስለሆነ ለዚህ ጥናት የተጠኚዎችን ድርሰት ለማረሚያ በመስፈርትነት ስራ ላይ ውሏል፡፡

በሌላ በኩል Heaton (1990) የጽህፈት ክሂልን ለመመዘን የሚያስችሉ ነጥቦችን እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡- ትክክለኛና ተገቢ የሆኑ አረፍተ-ነገሮችን መፃፍ፣ ተገቢውን ስርዓተ-ነጥብ በተገቢው ቦታ መፃፍ፣ ሀሳብን ቅደም ተከተላዊና ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ መግለጽ፣ ተገቢ የሆኑ የአፃፃፍ ስልቶችን በመጠቀም የአረፍተ-ነገርን ትክክለኛ አሰካክና የአንቀጽ አወቃቀር ስልትን በመጠቀም መፃፍ እና ጽሑፉ የሚቀርብላቸውን ተደራሲያን በማወቅ ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ተስማሚ የሆኑ ቃላትን በመምረጥና ሀሳብን ግልጽ በሆነ መንገድ የመግለጽ ችሎታ ሊታይ ይገባል በማለት ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂልን ለመመዘን ያስችል ዘንድ ቀጥሎ የቀረቡት ነጥቦች ወሳኝ ናቸው፡፡

### 2.1.8.1 የቃላት አመራረጥ

ሀሳብን በጽሑፍ አቀናብሮ ለማቅረብ የምንጠቀማቸው ቃላት ወሳኝ ናቸው። ጽህፈት እንደ ንግግር ወዲያውኑ ግብረ-መልስ የሚገኝበት ስላልሆነ የሚመረጡት ቃላት ምስል ካሳች፣ ሳቢ፣ ለአውድ ተስማሚና ለዛ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በመሆኑም አማረ (1986፣ 4) “ቃላት የደራሲ ቀኝ እጅ ናቸው። ደራሲ ያለ ቃላት ሌላ መሳሪያ የለውም። ጥረቱ ሊሳካም ሊከሽፍም የሚችለው ቃላትን በጥበብና በጥንቃቄ በመጠቀም ለቋንቋው ውበት ለማስገኘት ሲችል ነው” በማለት የቃላትን ጠቀሜታ አጽንኦት ሰጥተው አብራርተዋል። ይህም አባባል የሚያስገነዝበን አንድ ፀሐፊ ሀሳቡን በተገቢ መንገድ ለማስተላለፍ ከፈለገ ሲጽፍ፤ የሚመርጣቸው ቃላት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። የሚመረጡት ቃላት የዘዬ ችግር የሌለባቸው፣ እንግዳ ያልሆኑ፣ አሻሚነት የማይታይባቸው፤ የተሰለቹ ያልሆኑና መደበኛነት ያላቸው ቢሆኑ ጽሑፉ ተነባቢነት ሊኖረው ይችላል።

### 2.1.8.2 የአረፍተ-ነገር አወቃቀር

አንድ ፀሐፊ ሀሳቡን በጽሑፍ አማካኝነት ለማስተላለፍ ከፈለገ የቋንቋውን ትክክለኛ ህግና ስርዓት ተከትሎ መፃፍ አለበት። ሰዋስው እያንዳንዱን ቃላት እርስ በርሱ በማቀናጀት አረፍተ-ነገሮች የሚመሰረቱበት መንገድ ነው። ይህም ማለት ሰዋስው ሲባል ሀተታዊ፣ አፍራሽ ወይም ብዙ ቁጥር ወይም ጥያቄያዊ አረፍተ-ነገሮች ስንመሰርት የምንከተለው የቃላት አሰላለፍ ሁኔታ የሰዋስው ጉዳይ ነው በማለት Harmer (1994) ገልፀዋል። በመሆኑም አንድ ፀሐፊ ሀሳቡን ለመግለጽ ሲፈልግ በሚመሰርታቸው አረፍተ-ነገሮች ውስጥ ባሉት በባለቤትና ማሳሪያ አንቀጹ መካከል የቁጥር፣ የፆታ፣ የመደብና የተሳቢ አመልካች ቅጥያዎች ስምምነት ሊኖርና የቋንቋውን ስርዓት ጠብቆ መፃፍ አለበት።

### 2.1.8.3 የስርዓ-ተነጥብ አጠቃቀም

ስርዓተ-ነጥቦች አንድ ጽሑፍ የተፈለገውን መልዕክት በተገቢ ሁኔታ መግለጽ እንዲችሉ የሚደረጉ ምልክቶች ናቸው። ስርዓተ ነጥቦች በጽሑፍ ውስጥ የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለየት፣ ሀሳብን የሚያስተላለፉ አረፍተ-ነገሮች ማለቃቸውን ለማመልከት የፀሐፊውን ስሜት ለመግለጽና ወዘተ. ሊያገለግሉ ይችላሉ።

### 2.1.8.4 የአንቀጽ አወቃቀር

አንድ አንቀጽ ሀሳብን ለመግለፅ፣ ለማስረዳትና ለማብራራት በሚያስችሉ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮችና በአንድ ዋና አረፍተ-ነገር (ኃይለቃል) የሚገነባ የሀሳቦች ጥንቅር ነው፡፡ አንቀጹ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ ሊያንፀባርቅ የሚችለው በኃይለቃሉና በዝርዝር አረፍተ-ነገሮቹ መካከል የሀሳብ አንድነት ሲኖር ነው፡፡ በመሆኑም Pincas (1982, 55) "በአንቀጹ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች በተገቢው መንገድ እየተያያዙ አንዱን ሀሳብ ሊገልጹ የሚችሉ ሊሆን ይገባል" በማለት ሀሳቡን ያጠናክራሉ፡፡ አንድ የተዋጣለት አንቀጽ የአንቀጽ አንድነት፣ የአንቀጽ ቅንብር (ውህደት) እና የአንቀጽ ተያያዥነት የሚባሉ ሦስት ተፈላጊ ነገሮችን ማሟላት አለበት፡፡

#### 2.1.8.4.1 የአንቀጽ አንድነት

የአንቀጽ አንድነት ሲባል በአንቀጹ ውስጥ ባለው መንደርደሪያ አረፍ-ተነገር (ኃይለ ቃል) እና በሌሎች ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች መካከል የጠበቀ ትስስር አለ ማለታችን ነው፡፡ በአንቀጹ ውስጥ ያሉ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች የሚያብራሩትና የሚገልጹት ስለኃይለቃሉ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያም አንድ አንቀጽ ለመመስረት ሲታሰብ በቅድሚያ ኃይለቃሉን ወስኖ መነሳት ለአንቀጽ አንድነት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው Trimmer እና James (1988) ያብራራሉ፡፡

#### 2.1.8.4.2 የአንቀጽ ቅንብር /ውህደት/

የአንቀጽ ቅንብር ሲባል በጽሑፍ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ለማብራራትና ለማስረዳት የሚያስችሉ ነገሮችን ባህሪ በመረዳት እንደ ክብደትና ቅለታቸው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ስልት ነው፡፡ በአንቀጹ ውስጥ ያለውን መንደርደሪያ አረፍተ-ነገር መነሻ አድርጎ ሌሎች መንደርደሪያ አረፍተ-ነገሮችን የሚገልጹና የሚያከራክሩ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች በቅደም ተከተል ከክብደታቸውና ቅለታቸው አንፃር ከአቢይ ወደ ንዑስ ወይም ከንዑስ ወደ አቢይ እንደሚቀርቡ Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡

#### 2.1.8.4.3 የአንቀጽ ተያያዥነት

አንድን አንቀጽ የሚመሰርቱት አረፍተ-ነገሮች እርስበርሳቸው የተያያዙ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ አንቀጽን ሊመሰርቱ የሚችሉ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች እርስበርሳቸው በተገቢው ተያያዦች ተቀናጅተው ለአንባቢ በቀላሉ ሊተላለፍ የሚፈለገውን መልዕክት ሊረዳ ይገባዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በአንቀጹ ውስጥ ያሉ አረፍተ-ነገሮች እርስበርሳቸው የሚደጋገፉ፣ ቀድሞ

የሚመጣው አረፍተ-ነገር ለቀጣዩ ፍንጭ የሚሰጥ መሆን እንዳለበት Trimmer እና James (1988) ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በ2.1.8 የቀረቡት የጽህፈት ክሂል መመዘኛ ነጥቦች የዚህን ጥናት አላማ ከግብ የሚያደርሱና የድርሰት አፃፃፍን ቅርጽ በዝርዝር ስለሚያሳዩ በምሁራኑ በዝርዝር የተገለጹት መሠረተ-ሀሳቦች ተገቢና ተስማሚ እንደሆኑ አጥኝው ያምንበታል፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኝው ይህን ጥናት ለማዘጋጀት ከመነሳቱ በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ በውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍሎች እና በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረቡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናቶችን ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ባይሆኑም የአራት የምርምር ጥናቶች ተመሳሳይ ስራዎችን በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማግኘት ተችሏል፡፡ እነሱም ፡-

ሰይድ (1993) "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናት ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ጽህፈትን በተግባር እየተለማመዱ እንደማይማሩና የቢጤ እርማትም ተግባራዊ እንደማይሆን የገለጹ ሲሆን በጥናታቸው ውጤት ማጠቃለያ ላይ የጽህፈት ትምህርት ተግባር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡ በመሆኑም የተመራማሪው ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የጽህፈት ትምህርት አተገባበር ላይ ስለሚያተኩርና የዚህ ጥናት የሚያተኩረው የጽህፈት ችሎታን በንጽጽር በተግባር በመፈተሽ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ላይ ስለሆነ፤ እንዲሁም በክፍል ደረጃ፣ ጊዜና ቦታ ስለማይገናኝ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

አለማየሁ (1998) "አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁለት የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናት ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎች በጽህፈት ረገድ የተሻሉ መሆናቸውን ሲገልጹ የመፍትሄ ሀሳብ ብለው ያቀረቡት ከግል

ትምህርት ቤት ይልቅ በመንግስት ትምህርት ቤት ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽህፈትን አስመልክቶ ለተማሪዎች ተገቢ ትምህርት ሊሰጧቸው እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም የአለማየሁ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት በማጥናቱ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህን ጥናት ከእሳቸው ጥናት የሚለየው እሳቸው በ11ኛ ክፍል በሚማሩ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካካል ያለውን የጽህፈት ክሂል ችሎታ በማነጻጸር ውጤቱን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ የዚህ ጥናት ግን በኮሌጅ ደረጃ በአንድ በአማርኛ ትምህርት ክፍል አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት ሁለተኛ አመት ተማሪዎች ላይ ስለሚያተኩርና የሚጠናው ጥናት፣ በክፍል ደረጃ፣ ጊዜና ቦታ በጣም የተራራቀ በመሆኑ ከሳቸው ጥናት የተለየ ጥናት ያደርገዋል፡፡

ጌታቸው (2001) "በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ያቀረቡ ሲሆን በደብረ ማርቆስ ከተማ በሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ 8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በጽሑፍ ክሂል ችሎታ የትኞቹ እንደሚሻሉ ለማጥናት ሞክረዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎችን በተራ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግና ተማሪዎችንና መምህራንን የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ በ100 ሴትና በ100 ወንድ ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ወንድ ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል የተሻሉ መሆኑን በጥናታቸው አመልክቷል፡፡

ነገር ግን ይህ ጥናት በምዕራፍ አንድ ላይ Brekke David (2009)ን በመግለጽ ክሂሎች "የጾታ እኩልነት እየታየበት መጥቷል" የሚለውን ሀሳብ የጠቀሱ ቢሆንም በጥናቱ በተገኘው ውጤት መሠረት ሲቃወሙት ባለመታየቱ ጥናቱን ደካማ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በጽህፈት ክሂል ንጽጽራዊ ጥናት መሆኑ ካልሆነ በስተቀር በይዘትም ሆነ ይዞ ከተነሳ አላማና ውጤት ጋር በምንም መልኩ የሚገናኝ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የእሳቸው ጥናት የሚያተኩረው በደብረ ማርቆስ ከተማ ውስጥ የሚገኙ 8ኛ ክፍል የሴትና ወንድ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ንጽጽራዊ ጥናት ላይ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህ ጥናት ደግሞ በክፍል ደረጃ፣ ጊዜና ቦታ በጣም የተራራቀ እንዲሁም ፆታዊ መሰረት ላይ ብቻ ያደረገ ጥናት ባለመሆኑ ከእሳቸው ጥናት ይለያል፡፡

ኢሳያስ (2002) “የጽሑፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት አደረጃጀታቸው 10+2 የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ደብዳቤ ለመፃፍ ያላቸው ብቃት በጎባና ሮቤ መሰናዶ ትምህርት ቤት ናሙናነት” በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ያቀረቡ ሲሆን ጥናቱን ለማካሄድ አይነታዊና መጠናዊ ምርምሮችን በመጠቀም አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀምና ተማሪዎችን ደብዳቤ በማስፃፍ፣ መምህራንና ተማሪዎችን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት መረጃዎችን አሰባስበዋል፡፡ ከጥናቱም የተገኘው ውጤት በጽህፈት ትምህርት ሂደት ውስጥ የመሰናዶ ተማሪዎች መገንዘብ የሚገባቸውን የደብዳቤ አፃፃፍ እውቀት በተገቢው መንገድ ያልጨበጡና በትምህርት ቤት ሕይወታቸው ውስጥ የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያዎችንና ስልቶችን በትክክል ያልተረዱ መሆናቸውን በጥናት ውጤታቸው አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም የኢሳያስን ጥናት በምንመረምርበት ጊዜ ከርዕሱ ጀምሮ ችግር ያለበትና አጥጋቢ ያልሆነ ጥናት ነው፡፡ ርዕሱን በምናይበት ጊዜ 10+2 የሚለው አገላለጽ በአሁኑ በኢትዮጵያ ትምህርት ፖሊሲ 12ኛ ክፍልን አይገልጽም፡፡ ሊገልጽ የሚችለው 10ኛ ክፍል አጠናቀው ወደ ቅድመ ከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት (መሰናዶ) ያላለፉትንና በቴክኒክና ሙያ የሚሰለጥኑትን የ2ኛ አመት ተማሪዎችን የሚያመልክት ስያሜ ነው፡፡ እኔም የመጣልኝ ይህ ትርጓሜ ነበር፡፡ ነገር ግን ጥናታቸውን በጥልቀት ሳነበው በጥናቱ ውስጥ 12ኛ ክፍል የሚል ምትክ ስም ለማንበብ ችያለሁ፡፡ ይሁን እንኳ ብለን ስያሜውን ብንቀበለው 10ኛ ክፍል አጠናቀው በቴክኒክና ሙያ የሚሰለጥኑት 2ኛ አመት ተማሪዎችን ምን ስያሜ እንስጣቸው? ሌላው ደግሞ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩትን የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችንስ ምን እንበላቸው? መልሱን ለጥናቱ ባለቤት ትቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም አጥኝው የመረጠውን ስያሜ ትርጓሜ ማወቅና መረዳት የጥናቱ መጀመሪያ ነው ብየ አስባለሁ፡፡

ሌላው ደግሞ ጥናቱን ውጤት በምናይበት ጊዜ ብዙም ውሃ የሚያነሳ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የተገኘው ውጤት ከላይ እንደገለጽኩት “...የመሰናዶ ተማሪዎች መገንዘብ የሚገባቸውን የደብዳቤ አፃፃፍ እውቀት በተገቢው መንገድ ያልጨበጡና በትምህርት ቤት ሕይወታቸው ውስጥ የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያዎችንና ስልቶችን በትክክል ያልተረዱ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል” በማለት ያስረዳሉ፡፡ ይህ ማለት ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን አሰባስበውና አቅደው ለመጻፍ የማይቸገሩ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ከጥናቱ እንደምንረዳው ተማሪዎቹ የመፃፍ ችግር ሳይሆን ያለባቸው የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያዎችንና ስልቶችን አለማወቅ ነው፡፡ በሀገራችን ተማሪዎች

ላይ የሚታየውን የጽህፈት ችግር የማያሳይና የመፍትሄ ሀሳብ የማያቀርብ ምርምር ከመሆኑም በላይ አጥኚው ይዞት የተነሳውን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በዚህም የተነሳ ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በምንም መልኩ የማይገናኝ ጥናት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ቀደም ብዬ በዝርዝር በእያንዳንዱ ጥናት ስር በጠቀስኩት መልኩ የሰይድ (1993)፣ የጌታቸው (2001) እና የኢሳያስ (2002) ጥናቶች በስያሜም ይሁን በይዘት ከዚህ ጥናት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፡፡ ነገር ግን የአለማየሁ (1998) ጥናት በስያሜ የሚመሳሰል ሲሆን በአጠናን ዘዴው ግን የዚህ ጥናት ከእሳቸው ጥናት ይለያል፡፡ የሳቸው ጥናት የጽህፈት ችሎታን በመንግስትና በግል ትምህርት ቤት በሚማሩ ተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት ለማወቅ ያጠኑት ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ደግሞ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል በሚማሩ አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ በንጽጽር ማጥናት በመሆኑ ከእሳቸው ጥናት ይለያል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች በርዕስ፣ በተጠኝዎቹ የትምህርት ደረጃ፣ የጊዜ ርዝመትና የርዕስ አመራረጥ ከተጠቀሱት ጥናቶች በብዙ መልኩ እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነው፡፡ አጥኝው መረጃውን ሰብስቦ ያጠናው ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት መጠናዊ ምርምር እና በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር ስራ ላይ ውሏል፡፡

በዚህ ጥናት አጥኝው ቅይጥ የምርምር የተጠቀመበት ምክንያት ምርምሩ የሚተነተነው በቁጥር መረጃ ትንተናና በገለፃ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኝውም በቁጥር ለሚገልጸው የመረጃ ትንተና አመች ሆኖ ስላገኘው ሊመርጠው ችሏል፡፡ ሌላው በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ አይነታዊ ምርምር በቁጥር መረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በገለፃ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ስለዚህ በቁጥር ከሚተነተነው ውጭ ያለ መረጃ  አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አቀራረቡ ግን በገላጭ ንድፍ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኝው ቅይጥ የምርምር ዘዴን የሚከተለውን የ Cresswell, (2009) እና የያለው (2001) የምርምር መጻሕፍት ለጥናቱ መነሻ ግብዓትነት ተጠቅሟል፡፡

## 3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮ የሰነድ ፍተሻ፣ የተጠኝዎች የጽህፈት ክሂል ፈተና እና በተጠኝዎች ከሚሞላ ጽሑፍ መጠይቅ የሚገኙ የመረጃ ግብዓቶች ናቸው፡፡ እንዲሁም የንድፈ-ሀሳባዊ መሠረቶችና የድህረ-ምረቃ ጥናቶች፣ ድረ-ገጽና የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የጥናት መጻሕፍት ምርምር እና የተለያዩ ጆርናሎች ላይ በመመስረት ነው፡፡

በመሆኑም የሚፈለጉት መረጃዎች ተጠኝዎች ከፃፉት ድርሰት፣ ከጽሑፍ መጠይቅ፣ ከድህረ-ምረቃ ጥናቶች፣ ድረ-ገጽ፣ ጆርናሎችና የተለያዩ መጻሕፍት ላይ ከተሰበሰቡ በኋላ በአንድ ላይ በአስፈላጊው ቅደም ተከተል ተዘርዝረው የምክንያትና ውጤት ትንተና ተሰጥባቸዋል፡፡ አጥኝው ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተጠቀመባቸውን ዋቢ ጽሑፎች ምንጭ በእዚህ የምርምር ጥናት

መጨረሻ ላይ በዝርዝር ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ለዚህም መረጃነት አጥኚው የተጠቀማቸውን መረጃዎች በሙሉ ከጥናቱ መጨረሻ ላይ አባሪ አድርጎ አቅርቧል፡፡ ጥናቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚከተሉትን ነጥቦች ተከትሏል፡፡

ሀ. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም እና ኬኔዲ ቤተመጻሕፍት ከተመረጠው ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችን በማንበብ የአሠራር ዘዴውን ተከትሏል፡፡

ለ. ከተመረጡት መጻሕፍት ላይ የሚፈለጉትን መረጃዎች ሰብስቧል፡፡

ሐ. በተጨማሪም ከጽሕፈት ክሂል ትምህርት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተለያዩ ምሁራን ሥራዎች በማንበብ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመለየት ለትንተናው ተጠቅሟል፡፡

መ. በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ትንተና ተደርጓል፡፡

ሠ. ከተማሪዎች የተገኙት የመማር ማስተማር ጽሑፍ መጠይቅ ምለሰሾች እና የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ፈተናዎች ለጥናቱ ግብዓት ሆነው አገልግለዋል፡፡

## 3.3 የናሙና አወሳሰድ

የናሙና አወሳሰድን በተመለከተ በጥቅል ናሙና አወሳሰድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም የናሙና አወሳሰድ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት የጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኝ ብቸኛ የመምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በመሆኑና በትምህርት ክፍሉ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም ለአማራጭነት ሌላ ኮሌጅ የሌለ መሆኑ አጥኚው ጥቅል ናሙናን ተጠቅሞ ከ 31 ተማሪዎች መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚባሉት ጥናቱ እውን እንዲሆን ተገቢ መረጃዎች በአግባቡ የሚሰበሰብባቸው መንገዶችን የሚያብራራ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ለጥናቱ አስፈላጊና ተገቢ ናቸው ያላቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተከትሏል፡፡ እነሱም፡- የጽሕፈት ችሎታ ክሂልን የሚመዝኑ የጽሑፍ ፈተና እና በደጋፊነት የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቀጥለን እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመልከት፡፡

### 3.4.1 የጽህፈት ችሎታ መለኪያ ፈተና

የችሎታ መለኪያ ፈተና ስርዓተ-ትምህርቱን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ "የችሎታ መለኪያ ፈተና መሠረት የሚያደርገው የተዘጋጀ ስርዓተ-ትምህርትን፣ የመማሪያ መጻሕፍትንና የትምህርት ፕሮግራሞችን ነው" Hughes (2003, 12) በማለት ሀሳቡን ያጠናክሩታል፡፡ በተጨማሪም ይህ የፈተና አይነት መመስረት ያለበት ባለፈ የክፍል ልምምድ ላይ ሲሆን የመማር ማስተማሩ አንድ አካል ተደርጎ መታየት አለበት፡፡ አላማውም የትምህር ልምዶች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለመለየት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናትም መሠረት ያደረገው ተማሪዎች ቀደም ሲል የተማሩትንና የተለማመዱትን የጽህፈት ክሂል ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ማወቅ ስለሆነ የቀረበው የጽሕፈት ፈተና የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው፡፡ በዚህም መሠረት ተማሪዎች የተሰጧቸውን ርዕሶች መነሻ አድርገው አንዱን በመምረጥ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡

ሰንጠረዥ 1. ድርሰት እንዲጽፉ የተደረጉ ተማሪዎች ብዛት

| የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች | የተመረጠው ናሙና ብዛት | ፆታ | | ተጽፈው የተመለሱ ድርሰቶች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | |
| አማርኛ አፍፈት | 11 | 6 | 5 | 11 |
| አማርኛ ኢ-አፍፈት | 20 | 16 | 4 | 20 |

ከላይ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የሚማሩና ለጥናቱ በጥቅል ናሙና የተሳተፉ የመረጃ ሰጪ ሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ዝርዝር ነው፡፡ በመሆኑም በትምህርት ክፍሉ ሁለኛ አመት የሚማሩት ተማሪዎች በድምሩ 31 ሲሆኑ ወንዶቹ 22 ሴቶቹ ደግሞ 9 ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል 11 ተማሪዎች አማርኛ አፍፈት ሲሆኑ 20 ተማሪዎች ደግሞ ኢ-አፍፈት ናቸው፡፡

#### 3.4.1.1 የጽህፈት ፈተናው አዘገጃጀትና አቀራረብ

ተጠኝ ተማሪዎች የጽሕፈት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ድርሰት እንዲጽፉ ፈተና ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው አስር ርዕሶች መካካል አንዱን በመምረጥ ነፃ አፃፃፍ ስልትን ተከትለው ድርሰት ጽፈዋል፡፡ የተመረጡት ርዕሶች የተማሪዎችን የቀደመ የጽህፈት ልምድ ከግምት ውስጥ ያስገቡ የትምህርት ደረጃና መርሃ-ትምህርቱን

መሠረት ያደረጉና ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ ናቸው፡፡ ርዕሶቹ በሚያስተምሯቸው መምህራንና በጥናቱ አማካሪዬ ተገምግመው አስተያየትና ማሻሻያ ከተሰጠባቸው በኋላ የተመረጡ ናቸው፡፡ አስር ርዕሶች የሆኑበት ምክንያት ተማሪዎች በይበልጥ የሚያውቁትን ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ ታስቦ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በመረጡት አንድ ርዕስ ከ150-350 የሚደርሱ ቃላት በተሰጣቸው 90 ደቂቃዎች በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ድርሰት ጽፈዋል፡፡ ድርሰቱንም እንዲጽፉ የተደረገው አንድ ጊዜ ሲሆን 90 ደቂቃዎች ውስጥ በመረጡት ርዕስ ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓ፡፡ በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ የተደረገውም ተማሪዎቹ በሌሎች ሰዎች እንዳያስጽፉና በጥናቱ ላይ ተጽዕኖ እንዳያስከትል በማሰብ ነው፡፡

## 3.4.1.2 የጽህፈት ፈተናው አስተራረም

በዚህ ጥናት የተጠኝዎቹን የጽህፈት ችሎታ በአስተማማኝ መልኩ ለመለካት ያስችል ዘንድ ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች ሲታረሙ ስሜታዊነት እንዳይንፀባረቅባቸው አስፈላጊው ሁሉ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ይህን ስሜታዊነት ለመቀነስና የእርማቱን ስራ የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ የአራሚዎቹ ቁጥር ሶስት ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ሶስት የኮሌጁ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን እንዲሳተፉ በመድረግ ለተማሪዎቹ የተሰጠው ፈተና ታርሟል፡፡ ተማሪዎቹ የፃፉት ድርሰት ለአራሚዎች የተሰጡት እያንዳንዱ ድርሰት በሶስት ቅጂ ከተባዛ በኋላ ነው፡፡

የማረሚያ መስፈርቶቹም ከተፃፉት ድርሰቶች ጋር በማያያዝ ለአራሚዎቹ ተሰጥቷል፡፡ አራሚዎቹ የተገለገሉባቸው የማረሚያ መስፈርቶቹ የ Heaton (1990)ን የስህተት ቆጠራ ዘዴን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አራሚዎቹ ድርሰቶቹን ሲያርሙ በቅድሚያ ምን ምን መመዘኛ ነጥቦችን መመልከት እንዳለባቸው በምዕራፍ ሁለት በተጠቀሱት ክለሳ ድርሳናት ጽሑፎች ላይ በመመስረት የማረሚያ መመሪያና የድርሰት መመዘኛ ነጥቦች ከሚታረመው ድርሰት ጋር አብሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የአራሚዎች ዝርዝር መረጃ በሚከተለው ሰኝጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠዥ 2. ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት ያረሙ መምህራን ዝርዝር መረጃ የሚያሳይ

| ተ.ቁ. | የመምህራን የትምህርት ደረጃ | የተመረቁበት የትምህርት ዘርፍ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|
| 1 | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ በማስተማር ስነዘዴ | 13 ዓመት |
| 2 | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ በማስተማር ስነዘዴ | 12 ዓመት |
| 3 | የመጀመሪያ ዲግሪ | አማርኛ በማስተማር ስነዘዴ | 5 ዓመት |

ከላይ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ዝርዝርና የትምህርት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በትምህርት ክፍሉ በጠቅላላው አራት መምህራን ሲኖሩ አንዱ ትምህርት ላይ ይገኛል፡፡ ቀሪዎቹ ሶስት መምህራን ተጠኝ ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በማረም ለዚህ ጥናት የራሳቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም 2 መምህራን አማርኛን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸውና ከ 10 ዓመት በላይ በኮሌጁ በመምህርነት ያገለገሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም 1 መምህር አማርኛን በማስተማር የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና 5 ዓመት በመምህርነት ያገለገሉ ናቸው፡፡

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተነሱትን ጽንሰ-ሀሳቦች መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ መጠይቁ በድርሰት ፈተና የተገኘውን መረጃ የበለጠ ለማረጋገጥ፣ ለማጠናከርና ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት ታስቦ ተግባራዊ የሆነ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁም ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ስለመጠይቁ መግለጫ፤ የሁለተኛው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞላው ግለሰብ አስፈላጊ የሆኑ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ክፍል ሲሆን ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የጽህፈት ትምህርትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የሚይዝ ነው፡፡ የመጠይቁን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በሁለት የጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህራንና በጥናቱ አማካሪዬ ተገምግሞ የማሻሻያ ሀሳብ እንዲሰጥበት ከተደረገ በኂላ ተመሳሳይ ይዘት ያላው ጥያቄዎች እንዲወጡ ተደርጎ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም የጽሑፍ መጠይቁ ዝግ መጠይቅ ሲሆን አራት አማራጮችን የያዘ ነው፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን

### 3.5.1 የጽህፈት መረጃ አተናተን

ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች በሶስት አራሚዎች ከታረሙ በኋላ የሚታዩት ስህተቶች ማለትም የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የአረፍተነገር አወቃቀር፣ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም፤ የአንቀጽ አደረጃጀት፣ የፊደል አጣጣልና አጠቃቀም ወዘተ. ቀደም ሲል በተጠቀሱት የስህተት አይነቶች ስር እንደየስህተት አይነታቸው ተመዝግበዋል። ድርሰቱ ሲታረም አስተማማኝ እንዲሆን ለአንድ ተማሪ የሚመዘገበው ስህተት የሶስቱን አራሚዎች አማካኝ ውጤት በመውሰድ ነው። ቀጥሎም የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ አማርኛ አፍፈትና ኢአፍፈት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶች የቃላት ብዛት በመቁጠር ለድርሰቶቹ ብዛት ይካፈላል። ከዚያም የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ የፃፈባቸው የቃላት ብዛት ይታወቃል። ከዚያም አማካኝ ስህተቱን ለአማካኝ ቃላት በማካፈልና በ100 በማባዛት በአንድ ድርሰት ውስጥ የሰሩት ስህተቶች በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በዚህ ስሌት መሠረት አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶችን በማነፃፀር ትንተናው ተካሄዷል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በድርሰቶቹ ውስጥ ያለውን አማካይ የቃላት መጠን፣ አማካይ ስህተት፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ለማሳየት ሲባል Kroll (1990), *Kenworthy* (2006), *Staples* እና *Randi* (2016) የተጠቀሙበት ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል። የስሌት ቀመሩም እንደሚከተለው ነው።

- አማካይ የቃላት መጠን = $\frac{\text{ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች ቃላት ብዛት}}{\text{የተፃፉት ድርሰቶች ብዛት}}$
- አማካይ ስህተት = $\frac{\text{አጠቃላይ የስህተት ብዛት}}{\text{የተፃፉት ድርሰቶች ብዛት}}$
- አማካይ የስህተት ድግግሞሽ መጠን = $\frac{\text{አማካይ የስህተት ብዛት}}{\text{ለአማካይ ቃላት}} \times 100$

በመሆኑም አጥኚው በምዕራፍ አራት ላይ ለመረጃ ትንተና ከላይ የቀረበውን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ እና ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ላይ የቀረቡትን ንድፈ ሀሳቦች ጋር በሚዋሀድ መልኩ ከድርሰቶቹ በተገኙትና ከጽሑፍ መጠይቅ በተገኙት መረጃዎች ላይ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል።

### 3.5.2 የጽሑፍ መጠይቅ አተናተን

የጽሑፍ መጠይቁ ጠቀሜታው በተግባር በፃፉት ድርሰት ላይ የታዩት ስህተቶችና በጽሑፍ መጠይቁ የመለሱት ምን ያህል እውነታ እንዳለውና እንደሌለው በንጽጽር ለማየት ይጠቅማል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ ዝግ መጠይቅን የተከተለ ሲሆን ለትንተና የቀረቡት አራት አማራጮችን የያዙ 10 ጥያቄዎች ናቸው፡፡ አራት አማራጭ የሆነበት ምክንያት የመካከለኛው ለመወሰን እቸገራለሁ የሚለው አማራጭ ከየትኛውም ጋር መደመር ስለማይችል ለጥናቱ አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ ነው፡፡

በመሆኑም አራቱ አማራጮች በጥናቱ ወደ ሁለት በመክፈል ማለትም ፈጽሞ አልስማማምና አልስማማም ውጤታቸው ተመሳሳይ በመሆኑ በአንድ ላይ ተደምረዋል፡፡ እንዲሁም በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ በአንድ ላይ ተደምረው በእያንዳንዱ ጥያቄ ምልሽ የሰጡ ተጠኝዎች ብዛት ለጠቅላላ መላሾቹ ብዛት ተካፍሎ በመቶኛ በማስላት አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ለብቻ ተለይቶ በጥቅልና በጾታ ንጽጽራዊ ጥናት በማድረግ ትንተናው ተካሄዷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በናሙና ከተመረጡ ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን በምዕራፍ አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት አማርኛ ቋንቋ አፍፌትና ኢ-አፍፌት ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች በምዕራፍ ሁለት Pincas (1982) እና Heaton (1990)ን በመጥቀስ የቀረበውን የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ነጥቦችን መሠረት በማድረግ የተሰበሰበው የድርሰት መረጃና የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ እንደሚከተለው ንጽጽራዊ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 4.1. የቃላት አጠቃቀም

አማርኛ ቋንቋ አፍፌትና ኢ-አፍፌት ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶችን በማረም የታዩትን የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች ለመቁጠር ተሞክሯል፡፡ እንደስህተት የተመዘገበው ከዚህ በታች የቀረበውን ይመስላል፡፡

ሰንጠረዥ 3. የተጠኝ ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ችሎታን በተመለከተ ከፃፉት ድርሰት የተገኘ ውጤት፡፡

| የስህተት አይነት | አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
| | 11 | 1,925 | 175 | 464 | 42.18 | 24.1% | 20 | 2,135 | 106.75 | 1,281 | 64.05 | 60% |

ከሰንጠረዥ 3. መመልከት እንደሚቻለው የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች 1,925 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 464 ቃላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች 2,135 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 1,281 ቃላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አማርኛ ቋንቋ አፍፌት ተማሪዎች የተመዘገበባቸው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፌት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ ስለሆነ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ በመቀጠል አንድ ድርሰት የተፃፈበትን አማካይ ቃላት ብዛት ለማወቅ የተቆጠረውን የቃላት ብዛት ከድርሰቶቹ ቁጥር ጋር

በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያሉትን 1,925 ቃላት ለጠቅላላ ድርሰቶቹ (ለ11 ድርሰቶች) ስናካፍለው የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ በ175 ቃላት የተፃፈ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም የተመዘገቡትን ስህተቶች አማካይ ለማወቅ በስህተት የተመዘገቡትን ቃላት ለተፃፈው ድርሰት ብዛት ስናካፍለው 42.18 በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የተመዘገበ አማካይ ስህተት መሆኑ ታውቋል። ከዚህ በኋላ አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈልና በ100 በማብዛት የተመዘገበውን ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተችሏል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left| \frac{42.18}{175} \text{ X } 100 = 24.1\% \right|$$

እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶች አማካይ የቃላት ብዛት ለማወቅ ድርሰቶቹ የተፃፉበትን አጠቃላይ የቃላት ብዛት በመቁጠር ለድርሰት ቁጥሩ በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት በአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተፃፉት ድርሰቶች 2,135 ቃላት ሲኖራቸው ይህ ቁጥር ለ20 ድርሰቶች ሲካፈል አንድ ድርሰት በአማካይ በ106.75 ቃላት የተፃፈ መሆኑን ተረጋግጧል። በተጨማሪም በስህተትነት የተመዘገቡትን ቃላት ቁጥር ለድርሰቶቹ በማካፈል አማካይ ስህተትን ለማወቀ ተችሏል። በዚህም መሠረት በስህተትነት የተመዘገበው 1,281 ሲካፈል ለ20 ድርሰቶች አንድ ድርሰት በአማካይ በ 64.05 ቃላት ስህተት በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ መመዝገቡ ተረጋግጧል። በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left| \frac{64.05}{106.75} \text{ X } 100 = 60.4\% \right|$$

ከላይ ከተገኘው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተመዘገቡት ስህተቶች ሲነፃፀሩ አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 24.1% ያህሉ የቃላት አጠቃቀም ስህተት እንዳለባቸውና አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ 60.4% ያህል ስህተት እንዳለባቸው የተገኘው ውጤት ያሳያል። ከዚህም አንፃር አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች አነስተኛ ስህተት ስለተገኘባቸው በቃላት አጠቃቀም

ችሎታ የተሻሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የቃላት አጠቃቀም ችሎታ ከፆታ አንፃር ስንመለከት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ 4. የተጠኝ ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ችሎታ በፃፉት ድርሰት ከፆታ አንፃር የሚያሳይ መረጃ፡፡

| የስህተት አይነት | የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች | ፆታ | የድርሰት ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | አማርኛ አፍፈት | ወ | 6 | 1,140 | 190 | 228 | 38 | 20% |
| | | ሴ | 5 | 785 | 157 | 236 | 47.2 | 30% |
| | አማርኛ ኢ-ፍፈት | ወ | 16 | 1,865 | 116.56 | 522.2 | 32.64 | 28% |
| | | ሴ | 4 | 270 | 67.5 | 86.5 | 21.6 | 32% |

ከላይ ካለው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ውስጥ ወንዶች 28% ስህተት ሲፈጽሙ ሴቶቹ 32% ስህተት ተገኝቶባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃርም ወንዶቹ ከሴቶቹ ያስመገዘቡት ስህተት ትንሽ ስለሆነ በቃላት አመራረጥ ችሎታ የተሻሉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ውስጥ ወንዶች 20% ስህተት ሲገጥማቸው ሴቶቹ 30% ተመዝግቦባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ወንዶቹ በቃላት አመራረጥ ችሎታ ከሴቶቹ የተሻሉ እንደሆኑ ውጤቱ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ አማርኛ አፍፈትም ይሁኑ ኢ-አፍፈት ወንድ ተማሪዎች ከሴቶቹ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው በሁለቱም ፆታዎች መካከል የተደረገው የጥናት ውጤት ያመለክታል፡፡ ከቃላት አመራረጥ ጋር በተያያዘ ለተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 5. የተጠኝ ተማሪዎች የቃላት ምርጫን በተመለከተ መምህራን ያስተምሯቸው እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ መረጃ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት |
| የትምህርት ክፍሉ መምህራን በጽህፈት ወቅት ስለምጠቀምባቸው የተለያዩ የቃላት ምርጫ አስተምረውኛል | ፈጽሞ አልስማማም | 0 | 0% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 2 | 18.18% | 3 | 15% |
| | እስማማለሁ | 6 | 54.54% | 16 | 80% |
| | በጣም እስማማለሁ | 3 | 27.27% | 1 | 5% |

ከላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 81.81% የሚሆኑት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ስለቃላት አመራረጥ ሲያስተምሩ የቃላት አጠቃቀምና ምርጫን እንደሚያስተምሯቸው 18.18% የሚሆኑት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ እንደማያስተምሯቸው በሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 85% የሚሆኑት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ወቅት ስለሚጠቀሙባቸው የቃላት አጠቃቀምና ምርጫ እንደሚያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 15% የሚሆኑት ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ወቅት የቃላት አጠቃቀም ምርጫን እንደማያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆኑ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት መምህራን የቃላትን አጠቃቀምና ምርጫ እንደሚያስተምሯቸው ነው፡፡

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየው ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 4 በቀረበው የድርሰታቸው መረጃ ውጤት መሠረት 50% የሚሆን የቃላት አጠቃቀም ስህተት ሲታይባቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ በፃፉት ድርሰት 60% የሚሆን ስህተት ታይቶባቸዋል፡፡

በመሆኑም የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ መምህራንን ከመፍራት አኳያ የመለሱት ሊሆን ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የተሰጠው ምላሽ ከድርሰቶቻቸው ጋር ተያዥነት ያለውና ተገቢ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማስረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በአረፍተ-ነገሮቹ ውስጥ ጐላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም፡፡ በመሆኑም በጥናቱ መጨረሻ በምሳሌነት አጥኚው የተጠቀማቸውን አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶች በአባሪ "መ" ላይ እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎችን የፃፏቸውን ድርሰቶች በአባሪ "ሠ" ላይ ከጥናቱ ጋር ተያይዘው ይገኛሉ፡፡

## 1. አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች

### ሀ. የቃላት ድግግሞሽ እና ድረታ

- "---የተማረውን ትምህርት ወደቤት ሄደ በደንበ አሰላስሎ ያነባል በደንበ ያጠናል"
- "የሚሰጠው ጥቅም ቀላል አይደለም በዓለም ላይ እጅግ ጠቃሚ ነው-"
- "ከወዳሱዳን በኩል የመጡበታል መጥተውም የጋምቤለ ክልል ወደሱዳን ይሄዳሉ--"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች ያለባቸው ችግር የቃላት አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን የስርዓተ-ነጥብ ችግር፣ የሰዋስው ችግር፣የፊደል ግድፈትና ወዘተ. ችግሮች አሉባቸው፡፡ ነገር ግን ሌሎች ችግሮችን በቦታቸው ስለምናይ ከንዑስ ርዕሱ ጋር የሚሄደውን ችግር ቀጥለን እንመልከት፡፡

በቀረቡት ምሳሌዎች የተሰመረባቸው ቃላት የቃላት ድግግሞሽና ድረታ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ በድርሰት ትምህርታቸው ክፍለ ጊዜ በመምህራን ስለቃላት አጠቃቀምና ምርጫ ስለመማራቸው የሰጡት ምላሽ ይህን የሚያፈርስ ነው፡፡ በትክክል የተማሩ ቢሆን ኖሮ በምሳሌዎቹ ላይ የቀረቡትን ስህተቶች አይፈጽሙም ነበር፡፡ ስለዚህ መምህራን ስለቃላት አጠቃቀምና ምርጫ አስተምረውናል ያሉትን ከጥናቱ አንፃር የምንረዳው በሁለት መንገድ ነው፡፡ የመጀመሪያው መምህራንን ከመፍራት የመለሱት ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በዘፈቀደ መልስ ለመስጠት ብቻ ብለው የመለሱት ሊሆን እንደሚችል አጥኚው ይገምታል፡፡ በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ፡፡

- "---ወደ ቤት ሄዶ የተማረውን ትምህርት በደንብ ያጠናል።"
- "--- በዓለም ላይ የሚሰጠው ጥቅም ቀላል አይደለም።"
- "---ከሱዳን ወደ ጋምቤላ ክልል ይመጡበታል።

**ለ. ባዕድ ቃላት አጠቃቀም**

- "---የበት ስራም ሆነ ሌሎች <u>አሳይመንት</u> ነገር ለመስራት በግዘው እንደ ወጣ ወደ ቤት ነው የምሄደው።"
- "ጎበዝ ተማር <u>ለስማንት</u> <u>Time Table</u> የምሆነወን ያወጣል---"
- "ከለው የበርሃ አንፃር <u>ሻወር</u> ገብተን ንፀህ አየርተቀብለን እንመጣለን---"
- "--- በፊት ያጠናው ስለምጠፋ ወይንም አይምሮውን <u>ኮምፌውዝ</u> ስምያደርገው---"

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት እና የተሰመረባቸው ቃላት የአማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ባዕድ ወይም የውጭ ቃላት ናቸው። አንድ ቋንቋ መዋስን ብቸኛ አማራጭ የሚያደርገው በቋንቋው መግለጽ የማይችለውን ነገር ነው። ነገር ግን እነዚህ ባዕድ ቃላት በአማርኛ መተኪያ ያላቸውና ቋንቋውም መግለጽ የሚችል ሲሆን ተማሪዎቹ ይህን የመረጡበት ምክንያት የቋንቋ ችግር ስላለባቸውና እንግሊዘኛን መጠቀም ስልጣኔ መሰሏቸው እንደሁ መረዳት አያዳግትም። በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ ከባዕድ ቃላት የፀዱ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ።

- "--- እንደወጣ በጊዜ ወደ ቤቱ በመሄድ የቤት ስራ ይሰራል።"
- "ጎበዝ ተማሪ ለቤት ስራ የሚሆነውን ጊዜ ያቅዳል።"
- " ---ካለው በርሃ አንፃር ሰውነታችንን ታጥበን ንፁህ አየር እንቀበላለን።"
- "--- በፊት ያጠናው ጠፍቶበት እዳይደናገር---"

**2. አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች**

**ሀ. የቃላት ድግግሞሽ እና ድረታ**

- "የባሮ ወንዝ <u>ጥቅ</u> ለሰው ልጅ ብዙ <u>ጠቀሜታ</u> አለው"
- "ጎበዝ ተማሪ ለጥናት <u>ጊዜ</u> <u>ፓሮግሬሞ</u> አወጥቶ <u>የሞያጠናና</u> <u>የሞያነብ</u> ነው "
- "የዘፍ ጥቅም በጣም <u>አስፈላጊ</u> <u>አስፈላጊና</u> አሰሳቢነው"
- "---ብዙ <u>ጥቅም</u> <u>እየጠቀም</u> ስለሆ ባሮ <u>ይጠቅማል</u> ማራት ነው።"
- "ባር ወንዝ <u>ለመጋጋኘነት</u> ለ<u>ትራንስፖርት</u> አገልግሎት ይጠቀማሉ"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች ላይ የተሰመረባቸው ቃላት የቃላት ድግግሞሽና ድረታ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ በድርሰት ትምህርታቸው ክፍለ ጊዜ በመምህራን ስለቃላት አጠቃቀምና ምርጫ ስለመማራቸው የሰጡት ምላሽ ይህን የሚያፈርስ ነው፡፡ በትክክል የተማሩ ቢሆን ኖሮ በምሳሌዎቹ ላይ የቀረቡትን ስህተቶች አይፈጽሙም ነበር፡፡ ስለዚህ መምህራን ስለቃላት አጠቃቀምና ምርጫ አስተምረውናል ያሉትን ከጥናቱ አንፃር የምንረዳው በሁለት መንገድ ነው፡፡ የመጀመሪያው መምህራንን ከመፍራት የመለሱት ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በዘፈቀደ መልስ ለመስጠት ብቻ ብለው የመለሱት ሊሆን እንደሚችል አጥኚው ይገምታል፡፡ በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ፡፡

- "የባሮ ወንዝ ለሰው ልጅ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡"
- "ጎበዝ ተማሪ እቅድ አወጥቶ ያጠናል፡፡"
- "የዛፍ ጥቅም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡"
- "ባሮ ብዙ ጥቅም እየሰጠ ነው፡፡"
- "ባሮ ወንዝ ለመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል፡፡"

### ለ. ባዕድ ቃላት አጠቃቀም

- "---ሻወር ለመግባት በባሮ አጠገብ---"
- "---ለኢለትርኮ ሃይል ብቃት እንዳለው መንዝዙ ትልቅ ነው፡፡"
- "---እኛ ግን 5% ከበር ያደርጋ ብሌን አናስብም"

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት እና የተሰመረባቸው ቃላት የአማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ባዕድ ወይም የውጭ ቃላት ናቸው፡፡ አንድ ቋንቋ መዋስን ብቸኛ አማራጭ የሚያደርገው በቋንቋው መግለጽ የማይችለውን ነገር ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ባዕድ ቃላት በአማርኛ መተኪያ ያላቸውና ቋንቋውም መግለጽ የሚችል ሲሆን ተማሪዎቹ ይህን የመረጡበት ምክንያት የ አማርኛ ቋንቋ ቃላት ችግር ስላለባቸው እንደሁ መረዳት አያዳግትም፡፡ በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ ከባዕድ ቃላት የፀዱ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ፡፡

- "--- ባሮ ሰውነት ለመታጠብ----"
- "--- ወንዙ ትልቅ ስለሆነ መብራት ኃይል ማመንጫነት ብቃት አለው፡፡"
- "---እኛ ግን 5% ይሸፍናል ብለን አናስብም፡፡"

## 4.2. የአረፍተ-ነገር ሰዋሰዋዊነት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን በመቁጠር የሚከተለው መረጃ ተተንትኗል፡፡ ከላይ የተገለጹት ስህተቶች ለአሰራር ያመቹ ዘንድ በአንድ ክፍል በመመደብ ትንተና ተደርጓል፡፡ ስህተቶች ማለትም የፆታ፣ የቁጥር፣ የመደብ አጠቃቀም፣ የቃላትና ሀረጋት ቅንብሮችን በተመለከተ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 6. የተጠኝዎች አረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ በተመለከተ ከድርሰቶቻቸው የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| የስህተት አይነት | አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአረፍተነገር አወቃቀር | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
| | 11 | 1,925 | 175 | 73 | 6.64 | 3.79% | 20 | 2,135 | 106.75 | 203 | 10.15 | 9.5% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 73 የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ስህተቶች ሲቆጠሩ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ደግሞ 203 ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ በፊት የተሰራበትን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል፡፡ በዚሁም መሠረት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ ሰዋስዋዊ ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከድርሰት ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት 73 ለ11 ስናካፍለው 6.64 አማካይ ስህተት እናገኛለን፡፡ ተማሪዎቹ ድርሰት የፃፉባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 175 መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \Bigg| \quad \frac{6.64}{175} \times 100 = 3.79\% \quad \Bigg|$$

በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፉት ድርሰት ውስጥ 203 የሚሆኑ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ ስህተቶቹን ለድርሰቱ ቁጥር በማካፍል ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት 203 ለ20 ሲካል 10.15 አማካይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ድርሰት የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 106.75 ነው፡፡ በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left| \quad \frac{10.15}{106.75} \text{ X } 100 = 9.5\% \right|$$

ከላይ ባሉት የጥናት ውጤቶች መረዳት እንደተቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች 3.79% ሰዋስዋዊ ስህትት ሲገኝባቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ 9.5% ሰዋስዋዊ ስህትት ተገኝቶባቸዋል በመሆኑም በሰዋስዋዊ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታቸው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከኢአፍፊት ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆነ ያስመዝገቡት ስህተት ያመለክታል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ውስጥ የሚታየውን ሰዋስዋዊ ስህተት ከፆታ አንፃር እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 7. የተጠኝዎች የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ ከፆታ አንፃር የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| የስህተት አይነት | የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች | ፆታ | የድርሰት ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአረፍተነገር አወቃቀር (ሰዋስው) | አማርኛ አፍፊት | ወ | 6 | 1,140 | 190 | 33 | 5.5 | 3.5% |
| | | ሴ | 5 | 785 | 157 | 40 | 8 | 4.21% |
| | አማርኛ ኢ-ፍፊት | ወ | 16 | 1,865 | 116.56 | 155 | 9.69 | 8.31% |
| | | ሴ | 4 | 270 | 67.5 | 48 | 12 | 17.77% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታቸው ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ውጤቱ ያመለክታል፡፡ በሌላ መልኩ አማርኛ አፊፍት ወንድ ተማሪዎች 3.5% ያህል ስህተት

ሲገጥማቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ደግሞ 8.31% ያህል ስህተት እንደተመዘገበባቸው የመረጃው ውጤት ያመለከታል፡፡ ከዚህ አኳያም አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች የተሻለ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የሴት ተማሪዎችን ስህተት ስንመለከት አማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች 4.21% የሚሆን ስህተት ሲመዘገብባቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች 17.77% የሚሆን ስህተት ተመዝግቦባቸዋል፡፡ ከተመዘገበው የስህተት ድግግሞሽ አኳያም አማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች በአረፍተ-ነገር አወቀቀር ችሎታ የተሻሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከመረጃው ከተገኘው ውጤት በመነሳት አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች በሁለቱም ፆታዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻለ የአረፍ-ተነገር አወቃቀር ችሎታ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 8. ተጠኝዎች ድርሰት ሲጽፉ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታቸውን በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት |
| ድርሰትን ስጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እጠቀማለሁ | ፈጽሞ አልስማማም | 1 | 9.09% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 1 | 9.09% | 3 | 15% |
| | እስማማለሁ | 8 | 72.72% | 13 | 65% |
| | በጣም እስማማለሁ | 1 | 9.09% | 4 | 20% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 81.81% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደሚጠቀሙ የገለጹ ሲሆን 18.18% የሚሆኑት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደማይጠቀሙ የሰጡት መረጃ ያመልክታል፡፡

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 85% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 15%

የሚሆኑት ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፈትም ሆኑ ኢአፍፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደሚጠቀሙ መግለፃቸውን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየውን ተመሳሳይነት አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 8 የሰጡት መረጃ ከኢ-አፍፈት ተማሪዎች አንፃር ተዓማኒነት አለው ለማለት ያስችላል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍፈት ተማሪዎች የተሻለ የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትክክል እንዳልሆነ ከድርሰቶቻቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር (ሰዋስው) ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማስረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በአረፍተ- ነገሮቹ ውስጥ ጎላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም፡፡ በመሆኑም  በጥናቱ መጨረሻ በምሳሌነት አጥኚው የተጠቀማቸውን አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በአባሪ "መ" ላይ እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎችን የፃፉትን ድርሰት በአባሪ "ሠ" ላይ ከጥናቱ ጋር ተያይዘው ይገኛሉ፡፡

### 1. አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የሰዋስው ስህተቶች

### ሀ. የቁጥር ስምምነት ችግር

- "ለሰውልጅ ያለዛፍመኖር አይችሉም"
- "የባሮ ጥቅሙ አሁንም እግ በጣም ብዙ ናቸው"
- "ለጋምበለ የሉት ህዝብ ሁሉ የሚያገለግልውሃ ነው"
- "ዛፎች የተለያዩ ጥቅሞች አሉ"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የቁጥር ስምምነት ችግር ብቻ ያለባቸው ሳይሆኑ የአረፍተ-ነገር ሰዋስው፣ የስርዓተ-ነጥቦች ችግር፣ የፊደል ግድፈትና ወዘተ. ችግር

ያለባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን የተገለጹት ችግሮች በሚፈቅደው ቦታ ወደ ፊት ስለሚነሱ ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት፡፡

በመሆኑም የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር "ለሰውልጅ ያለዛፍመኖር አይችሉም" የሚለው የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር ስምምነት ችግር ይታይበታል፡፡ መሆን የነበረበት "የሰው ልጅ ያለ ዛፍ መኖር አይችልም፡፡" ወይም "የሰው ልጆች ያለ ዛፍ መኖር አይችሉም፡፡" በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ችግሮቹ ይቀረፉ ነበር፡፡ ሁለተኛው አረፍተ-ነገር ደግሞ "የባሮ ጥቅሙ አሁንም እግ በጣም ብዙ ናቸው" የሚል ሲሆን ይህ አረፍተ-ነገር የፊደል ግድፈት፣ አላስፈላጊ የቃል ጭማሪ መግባትና የስርዓተ-ነጥብ ችግር አለበት፡፡ ነገር ግን ለምሳሌ ከቀረበበት ርዕስ ጋር የሚገናኘው ችግር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር አለመስማማት ነው፡፡ መሆን የነበረበትም "የባሮ ጥቅም እጅግ በጣም ብዙ ነው፡፡" ወይም "የባሮ ጥቅሞች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው፡፡" በዚህ መንገድ ቢስተካከል ችግሮቹ ይቀረፉ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም በምሳሌነት የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች ከላይ ሁለቱ ምሳሌዎች በቀረቡት መሠረት ሁሉም ተመሳሳይ ችግሮች ያሉባቸው አረፍተ-ነገሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ፡፡

- "የሰው ልጅ ያለ ዛፍ መኖር አይችልም፡፡ (የሰው ልጆች ያለ ዛፍ መኖር አይችሉም፡፡)"
- "የባሮ ጥቅም እጅግ በጣም ብዙ ነው "
- "ለጋምቤላ ህዝቦች የሚያገለግል ውሃ ነው፡፡"
- "ዛፎች የተለያዩ ጥቅሞች አሏቸው፡፡"

### ለ. የመደብ አጠቃቀም ችግር

አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የመደብ አጠቃቀም ችግሮች አልታዩባቸውም፡፡ ይህም የሚያሳየን በድርሰት አፃፃፍ አይሳሳቱም ማለት ሳይሆን ድርሰቱን የፃፉት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በንግግር ጊዜ የመደብ አጠቃቀምን በደንብ አውቀው ስለሚጠቀሙት በድርሰታቸውም ይህ ሁኔታ ጠቅሟቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

## ሐ. የቃላት ቅደም ተከተል ችግር

የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ማለት አንድ ቃል በተገቢው ቦታና የሚገባበትን የቦታ ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ መጠቀም ማለት ነው፡፡

- “የሚሰጠው ጥቅም ቀላል አይደለም በዓለም ላይ እጅግ ጠቃሚ ነው የምንለው ወንዝ ነው፡፡”
- “የባሮ ወንዝ ጠቀሜታ ስንመለከት በጋምቤላ ካለው የሙቀት አንፃር ይህ ወንዝ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ጥቅም መስጠቱ ይታወቃል፡፡”
- “በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የበረሃ አይነት እጅግ በጣም ከባድነው”

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የተለያዩ የሰዋስው ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት፡፡

በመሆኑም የመጀመሪውን ምሳሌ ብናይ “የሚሰጠው ጥቅም ቀላል አይደለም በዓለም ላይ እጅግ ጠቃሚ ነው የምንለው ወንዝ ነው፡፡” የሚለው አገላለጽ ለንግግር ቢሆን ሊያግባባ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ አቀባይና ተቀባይ አብረው መልዕክቱን ስለሚቀባበሉ ማስተካከያ በማድረግ መልዕክቱን መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በጽህፈት ጊዜ መልክት አቀባዩና ተቀባዩ አብረው ስለማይገናኙና የቋንቋው ሰዋስው ስለማይፈቅድ በዚህ መልኩ መጠቀም ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መልዕክቱ በቀላሉ ለመልዕክት ተቀባዩ እንዳይተላለፍ እክል ይገጥመዋል፡፡ ስለዚህ ይህ አረፍተ-ነገር መፃፍ የሚገባው “በዓለም ላይ ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር እጅግ በጣም ጠቃሚ ወንዝ ነው፡፡” በሚል መቅረብ አለበት፡፡

ሁለተኛው አረፍተ-ነገር ደግሞ “የባሮ ወንዝ ጠቀሜታ ስንመለከት በጋምቤላ ካለው የሙቀት አንፃር ይህ ወንዝ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ጥቅም መስጠቱ ይታወቃል፡፡” የሚለው “ በጋምቤላ ካለው ሙቀት አንፃር የባሮ ወንዝ የሚሰጠው ጠቀሜታ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡” በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ ሁሉንም ያግባባ ነበር፡፡ ሶስተኛው አረፍተ-ነገር የስርዓተ-ነጥብ ችግር፣ አላስፈላጊ የቃላት ጭመራና የመሳሰሉት ችግሮች ይታዩበታል፡፡ ሆኖም ከርዕሱ ጋር የሚሄደውን የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ስናይ “በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የበረሃ አይነት እጅግ በጣም ከባድነው” የሚለው በአረፍተ-ነገሩ መተላለፍ የተፈለገው መልዕክት አገላለጽ ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በርሃ በአይነት አይገለጽም፡፡ ስለዚህ “የጋምቤላ ክልል በረሃ እጅግ በጣም ከባድ ነው” በሚል ተስተካክሎ ቢቀርብ ሁሉንም ተደራሲ ሊያግባባ ይችላል፡፡

## 2. አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የሰዋስው ስህተቶች

### ሀ. የቁጥር ስምምነት ችግር

- "ባሮ ዘረያ እስከ ሶዳን ድሶር ያለች ስወች---"
- "ዛፎች ብዙ ጥቅሞች አሉት"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የቁጥር ስምምነት ችግር ብቻ ያለባቸው ሳይሆኑ የአረፍተ-ነገር ሰዋስው፣ የስርዓተ-ነጥቦች ችግር፣ የፊደል ግድፈትና ወዘተ. ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን የተገለጹት ችግሮች በሚፈቅደው ቦታ ወደፊት ስለሚነሱ ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት፡፡

በመሆኑም የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር "ባሮ ዘረያ እስከ ሶዳን ድሶር ያለች ስወች---" የሚለው የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር ስምምነት ችግር ይታይበታል፡፡ መሆን የነበረበት "በባሮ ዙሪያ እስከ ሱዳን ድረስ ያሉ ሰዎች---" በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ችግሮቹ ይቀረፉ ነበር፡፡ ሁለተኛው አረፍተ-ነገር ደግሞ "ዛፎች ብዙ ጥቅሞች አሉት" የሚል ሲሆን ይህ አረፍተ-ነገር የስርዓተ-ነጥብ ችግር አለበት፡፡ ነገር ግን ለምሳሌ ከቀረበበት ርዕስ ጋር የሚገናኘው ችግር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር አለመስማማት ነው፡፡ መሆን የነበረበትም "ዛፎች ብዙ ጥቅሞች አሏቸው፡፡" ወይም "ዛፍ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡" በዚህ መንገድ ቢስተካከል ችግሮቹ ይቀረፉ ነበር፡፡

### ለ. የመደብ አጠቃቀም ችግር

- "የጋምበለ ወሶጥ የለወ ሶወች ሁለ ባሮ ባሮ ባይኖ መኖ አልችልም፡፡"
- "የባሮ ደር የለው መንጎ ወኃ ባይኖር መኖ መኖ መቆ አልችልም፡፡"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢአፍፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የመደብ አጠቃቀም ችግር ብቻ ያለባቸው ሳይሆኑ የአረፍተ-ነገር ሰዋስው፣ የስርዓተ-ነጥቦች ችግር፣ የፊደል ግድፈት፣ የቁጥር ስምምነት ችግር፣ የቃል ድግግሞሽ እና ወዘተ. ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት፡፡

በመሆኑም ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ላይ የተሰመረባቸው ቃላት የመደብ አመልካች ቅጥያዎችና የማሰሪያ አንቀጹ የተስማሙ አይደሉም፡፡ ቀጥለን አንዱን በምሳሌነት እንመልከት፡፡ የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር "የጋምበለ ወሶጥ የለወ ሶወች ሁለ ባሮ ባሮ ባይኖ መኖ አልችልም፡፡" የሚል ሲሆን አረፍተ-ነገሩ ቀደም ሲል ከላይ የጠቀስኳቸው ችግሮች በሙሉ ያሉበት ነው፡፡ ስለዚህ የድርሰቱ ፀሐፊ መፃፍ የፈለገው "የጋምቤላ ውስጥ ያለው ሰዎች ሁሉ ባሮ ባይኖር መኖር አልችልም፡፡" ለማለት ፈልጎ ነው፡፡ ይህም አረፍተ-ነገር የተስተካከለ ባይሆንም ከመጀመሪያው የተሻለ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ "ያለው" የሚለው ቃል ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥርን ያመለክተናል፡፡ "አልችልም፡፡" በአረፍተ-ነገሩ መጨረሻ ላይ የተሰመረበት የማሰሪያ አንቀጽ ቃል ደግሞ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አመልካች ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ተጣጥመው አይሄዱም፡፡ በዚህም የተነሳ የመደብ ቁጥር ስምምነት ችግር አለበት፡፡ በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ፡፡

- "በጋምቤላ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ያለ ባሮ መኖ አይችሉም፡፡"
- "የባሮ ዳር ያለው ማንነ ያለ ውኃ መኖር  አይችልም፡፡"

## ሐ. የቃላት ቅደም ተከተል ችግር

የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ማለት አንድ ቃል በተገቢው ቦታና የሚገባበትን የቦታ ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ መጠቀም ማለት ነው፡፡

- "ያለዛፍ መኖር በጣም ይከብዳል ለሰው ልጅ፡፡"
- "ብርቅዬ እንስሳቶችን ለማገኛት ወይም በማረባት በቂ የሆነ ደን መኖር አለበት በአካባቢያችን፡፡"
- "የዘፍ ጥቅም ተወርቶና ተናግሮ አያልቅም ብየእገምታለሁ በበኩሌ፡፡"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምሳሌዎቹ የተለያዩ የሰዋስው ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት፡፡ የመጀመሪውን ምሳሌ ብናይ "ያለዛፍ መኖር በጣም ይከብዳል ለሰው ልጅ፡፡" የሚለው አገላለጽ ለንግግር ቢሆን ሊያግባባ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ አቀባይና ተቀባይ አብረው መልዕክቱን ስለሚቀባበሉ ማስተካከያ በማድረግ መልዕክቱን መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በጽህፈት ጊዜ መልክት አቀባዩና ተቀባዩ

አብረው ስለማይገናኙና የቋንቋው ሰዋስው ስለማይፈቅድ በዚህ መልኩ መጠቀም ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መልዕክቱ በቀላሉ ለመልዕክት ተቀባዩ እንዳይተላለፍ እክል ይገጥመዋል፡፡

ስለዚህ ይህ አረፍተ-ነገር መፃፍ የሚገባው "የሰው ልጅ ያለ ዛፍ መኖር በጣም ይከብደዋል፡፡" በሚል መቅረብ አለበት፡፡ ሁለተኛው ደግሞ "ብርቅዬ እንስሳቶችን ለማገኛት ወይም በማረባት በቂ የሆነ ደን መኖር አለበት በአካባቢያችን፡፡" የሚለው "በአካባቢያችን ብርቅዬ እንስሳቶችን ለማግኘት ደን መኖር አለበት፡፡" በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ ሁሉንም ያግባባ ነበር፡፡ ሶስተኛው አረፍተ-ነገር የስርዓተ-ነጥብ ችግር፣ የፊደል ግድፈት፣ የቃላት ድረታና የመሳሰሉት ችግሮች ይታዩበታል፡፡ ሆኖም ከርዕሱ ጋር የሚሄደውን የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ስናይ ባለቤቱ ማሰሪያ አንቀጽ ላይ ማሰሪያ አንቀጹ ደግሞ ባለቤት ላይ በመምጣቱ ተገቢውን ቅደም ተከተል አልጠበቀም፡፡ ስለዚህ " እኔ በበኩሌ የዛፍ ጥቅም ተነግሮ አያልቅም አስባለሁ፡፡" በሚል መልኩ ቢስተካከል የሰዋስው ስርዓቱን የተከተለ ይሆናል፡፡

## 4.3. የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች በመቁጠር የሚከተለው መረጃ ተተንትኗል፡፡

ሰንጠረዥ 9. የተጠኝዎች የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም በተመለከተ ከድርሰቶቻቸው የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| የስህተት አይነት | አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
| | 11 | 1,925 | 175 | 195 | 17.72 | 10.13% | 20 | 2,135 | 106.75 | 209 | 10.45 | 9.79% |

ከላይ በቀረበው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 195 የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ሲቆጠሩ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ደግሞ 209 ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ በፊት የተሰራበትን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል፡፡ በዚሁም መሠረት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ

የፈጸሙት አማካይ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከድርሰት ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት 195 ለ11 ስናካፍለው 17.72 አማካይ ስህተት እናገኛለን፡፡ ተማሪዎቹ ድርሰት የፃፉባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 175 መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \frac{17.72}{175} \times 100 = 10.13\%$$

በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፉት ድርሰት ውስጥ 209 የሚሆኑ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለድርሰቱ ቁጥር በማካፍል ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት 209 ሲካል ለ20 10.45 አማከይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ድርሰት የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 106.75 ነው፡፡ በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \frac{10.45}{106.75} \times 100 = 9.79\%$$

ከላይ ካሉት የመረጃ ውጤቶች መገንዘብ እንደተቻለው አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ከአፍፊት ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያስመዘገቡት ስህተት ያመላክታል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች 10.13% የስርዓተ-ነጥብ ስህተቶችን ሲያስመዘግቡ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ 9.79% የስርዓተ-ነጥብ ስህተቶችን በማስመዝገባቸው በጥናቱ ውጤት መሠረት አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ያመለክተናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎች በፃፉት ድረሰት ውስጥ የሚታየውን ሰዋስዋዊ ስህተት ከፆት አንፃር እንመለከት፡፡

ሰንጠረዥ 10. የተጠኝ ተማሪዎች የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ከፆታ አንፃር የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| የስህተት አይነት | የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች | ፆታ | የድርሰት ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም | አማርኛ አፍፊት | ወ | 6 | 1,140 | 190 | 79 | 13.17 | 6.93% |
| | | ሴ | 5 | 785 | 157 | 116 | 23.2 | 14.77% |
| | አማርኛ ኢአፍፊት | ወ | 16 | 1,865 | 116.56 | 177 | 11.06 | 9.49% |
| | | ሴ | 4 | 270 | 67.5 | 32 | 8 | 11.85% |

ከላይ በሰንጠረዥ 10 በቀረበው የጥናት ውጤት መሠረት ለመረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆነ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ከሴቶቹ የተሻሉ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች 6.93% ያህል ስህተት ሲገጥማቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ደግሞ 9.49% ያህል ስህተት እንደተመዘገበባቸው የመረጃው ውጤት ያመለክታል፡፡ ከዚህ አኳያም አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች የተሻለ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የሴት ተማሪዎችን ስህተት ስንመለከት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች 14.77% የሚሆን ስህተት ሲመዘገብባቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች 11.85% የሚሆን ስህተት ተመዝግቦባቸዋል፡፡ ከተመዘገበው የስህተት ድግግሞሽ አኳያም አማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች ከአማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታ የተሻሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከመረጃው ከተገኘው ውጤት በመነሳት አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻለ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 11. ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት |
| የትምህርት ክፍሉ መምህራን ስለአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም አስተምረውኛል | ፈጽሞ አልስማማም | 0 | 0% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 0 | 0% | 1 | 5% |
| | እስማማለሁ | 2 | 18.18% | 9 | 45% |
| | በጣም እስማማለሁ | 9 | 81.81% | 10 | 50% |

ከላይ ከቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች 100% መምህራን በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደሚያስተምሯቸው በሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 95% የሚሆኑት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደሚያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 5% የሚሆኑት ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደማያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆኑ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት መምህራን በጽሕፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደሚያስተምሯቸው ነው፡፡

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየው ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፍፊትም ይሁን ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ላይ የታየው የስርዓተ-ነጥብ ችግር የአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችን አያውቁም የሚያስብል ነው፡፡ በመሆኑም የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ መምህራንን ከመፍራት አኳያ የመለሱት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የተሰጠው ምላሽ ከድርሰቶቻቸው ጋር ተያዥነት ያለውና ተገቢ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማስረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በአረፍተ- ነገሮቹ ውስጥ ጉላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር

በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም፡፡ በመሆኑም በጥናቱ መጨረሻ በምሳሌነት አጥኚው የተጠቀማቸውን አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በአባሪ "መ" ላይ እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎችን የፃፉትን ድርሰት በአባሪ "ሠ" ላይ ከጥናቱ ጋር ተያይዘው ይገኛሉ፡፡

## 1. አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቃም ችግሮች

## ሀ. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች

- "---ለእንስሳት መጠጫ ይሆናል_"
- "ነበዝ ለራሱም ሆነ ለሀገሩም ተፈላጊ ነው_"
- "ዛፍጥቅምብዙነው_"
- "በረሃ የሚባለው ነገር በጣም የሚያስፈራ ነገር ነው_"

ከላይ በምሳሌዎች የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች የተወሰዱ ሲሆን ያለባቸውን ሰዋስዋዊ ችግሮች ትተን ሁሉም በአረፍተ-ነገራቸው መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ አልተጠቀሙም፡፡ ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ የስረዓተ-ነጥቦችን ጥቅም ካለመረዳትና አጠቃቀማቸውንም ካለማወቅ የመነጨ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ይጠቁመናል፡፡

## ለ. የሁለት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች

- "የዛፍጥቅምብዙነው"
- "ዛፍየአፈርመሸርሸርእንዳይከሰት---"
- "ለነብር ለአንበሳ ለድኩላ ለጦጣ ለዝሆን ለጀብ---"
- ወይ ይህ ሀገር በጣም በረሃ ነው እዚህ ማን ይኖራል ይላሉ
- በረሃ ላይ ከሁለት ዓመት በላይ የቆየ ሰው ለምስክርነት አይበቃም

ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች በንዑስ ርዕሱ እንደተጠቀሰው የሁለት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች የሚታዩባቸው አረፍተ-ነገሮች ናቸው፡፡ መሆኑም የመጀመሪያውና ሁለተኛው አረፍተ-ነገሮች የሁለት ነጥብ አጠቃቀም ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ በኮምፒውተር ጽህፈት ጊዜ ለሁለት ነጥብ ቦታ እየተው መፃፍ ይቻላል፡፡ በእጅም ጽህፈት ቢሆን እንዲሁ ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በዚህ መንገድ መጠቀም አረፍተ-ነገሮቹን አንብቦ ለመረዳት በጣም ያስቸግራል፡፡

ሌላው ደግሞ ሦስተኛው አረፍተ-ነገር ዝርዝር ነገሮችን የያዘ ሲሆን ነጠላ ሰረዝ መጠቀም ሲኖርባቸው አልተጠቀሙም። አራተኛውና አምስተኛው አረፍተ-ነገሮች በድርሰታቸው ላይ የጻፉት የሰውን ሀሳብ ወይም ንግግር በመሆኑ በጥቅስ ምልክት መቀመጥ ነበረባቸው። ነገር ግን ድርሰቱን የጻፉት ከላይ በምሳሌው እንደተቀመጠው ነው። ከአንድ እስከ ሶስት ያሉትን አጥኝው በጥቅስ ምልክት ያስቀመጠው በምሳሌነት የተወሰደ የሌሎች ሀሳብ በመሆኑ ነው። ሆኖም የመጨረሻው በጥቅስ ምልክት ውስጥ ያልገባው በቀረበበት መንገድ እንዳለ ለማሳየት ታስቦ ነው። በመሆኑም ሁሉም እንደሚከተለው ተስተካክለው መፃፍ ነበረባቸው።

- "የዛፍ ብዙ ጥቅም አለው"
- "ዛፍ የአፈር መሸርሸር እንዳይከሰት---።"
- "ለነብር፣ ለአንበሳ፣ ለድኩላ፣ለጦጣ፣ ለዝሆን፣ ለጅብ፣---።"
- "ወይ ይህ ሀገር በጣም በረሃ ነው እዚህ ማን ይኖራል ይላሉ"
- "በረሃ ላይ ከሁለት ዓመት በላይ የቆየ ሰው ለምስክርነት አይበቃም"

2. **ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቃም ችግሮች**

**ሀ. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች**

- "የባሮ ወንዝ ጠቀሜታ ይበልጥ አለው_"
- "ጎበዝ ተማሪ ለጥናት ጊዜ ፓርግረሞ አወጥቶ የሞያጠናና የሞያነብ ነው_"
- "ዞፍ በሁለት ዓይነት መልኩ ማየት እንችላሌን_"
- "ያለ ዛፍ መኖር በጣም ይከብዳል_"

ከላይ በምሳሌዎች የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች የተወሰዱ ሲሆን ያለባቸውን ሰዋስዋዊ ችግሮች ትተን ሁሉም በአረፍተ-ነገራቸው መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ አልተጠቀሙም። ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ የስረዓተ-ነጥቦችን ጥቅም ካለመረዳትና አጠቃቀማቸውንም ካለማወቅ የመነጨ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ይጠቁመናል። ነገር ግን ከአማርኛ አፍፈት ተማሪዎች አንፃር ሲነፃፀሩ አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር ሁሉም በፃፏቸው ድርሰቶች ላይ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀማቸው በጣም የተሻለ ነው። ስለዚህ የስርዓተ-ነጥቦችን አጠቃቀም ያውቃሉ ማለት ያስችላል።

**ለ. የሁለት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች**

- "---አስፈላጊና አሳሳቢነው_"
- ላያስችል አይሰጥም
- ጋምቤላ ደግሞ ሀገር ነው እንዴ

ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች በንዑስ ርዕሱ እንደተጠቀሰው የሁለት ነጥብና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች የሚታዩባቸው አረፍተ-ነገሮች ናቸው፡፡ መሆኑም የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር የሁለት ነጥብና የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግር ያለበት ነው፡፡ በኮምፒውተር ጽህፈት ጊዜ ለሁለት ነጥብ ቦታ እየተው መፃፍ ይቻላል፡፡ በእጅም ጽህፈት ቢሆን እንዲሁ ማድረግ ይቻላል፡ ፡ ነገር ግን በዚህ መንገድ መጠቀም አረፍተ-ነገሩን አንብቦ ለመረዳት በጣም ያስቸግራል፡፡

ሁለተኛውና ሶስተኛው አረፍተ-ነገሮች በድርሰታቸው ላይ የጻፉት የሰውን ሀሳብ ወይም ንግግር በመሆኑ በጥቅስ ምልክት መቀመጥ ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ድርሰቱን የጻፉት ከላይ በምሳሌው እንደተቀመጠው ነው፡፡ የመጀመሪያውን አአረፍተ-ነገር አጥኚው በጥቅስ ምልክት ያስቀመጠው በምሳሌነት የተወሰደ የሌሎች ሀሳብ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም የመጨረሻዎቹ ሁለቱ በጥቅስ ምልክት ውስጥ ያልገቡት በቀረበበት መንገድ እንዳለ ለማሳየት ታስቦ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም እንደሚከተለው ተስተካክለው መፃፍ ነበረባቸው፡፡

- "---አስፈላጊና አሳሳቢ ነው፡፡"
- "ላያስችል አይሰጥም"
- "ጋምቤላ ደግሞ ሀገር ነው እንዴ"

## 4.4. የአንቀጽ አደረጃጀት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያለውን የአንቀጽ አንድነት፣ የአረፍተ-ነገር ተያዥነትና ዝምድና፣ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ የተገኘውን ጥናታዊ ውጤት ቀጥሎ በቀረበው መልኩ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ሰንጠረዥ 12. የተጠኙ ተማሪዎች የአንቀጽ አደረጃጀትን በተመለከተ ከድርሰቶቻቸው የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ።

| የስህተት አይነት | አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአንቀጽ አደረጃጀት | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
| | 11 | 1,925 | 175 | 39 | 5.54 | 2.03% | 20 | 2,135 | 106.75 | 88 | 4.4 | 4.12% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 39 የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ሲቆጠሩ አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ደግሞ 88 ስህተቶች ተቆጥረዋል። በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ ቀደም ሲል የተሰራበትን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል። በዚሁም መሠረት አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከድርሰት ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 39 ለ11 ስናካፍለው 5.54 አማካይ ስህተት እናገኛለን። ተማሪዎቹ ድርሰት የፃፉባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 175 መሆኑ ይታወቃል። በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \Bigg| \quad \frac{5.54}{175} \text{ X } 100 = 2.03\% \quad \Bigg|$$

በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በተሰራው መልኩ ተሰልቷል። በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፉት ድርሰት ውስጥ 88 የሚሆኑ የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል። የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለድርሰቱ ቁጥር በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 88 ለ20 ሲካል 4.4 አማከይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል። ድርሰት የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 106.75 ነው። በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \qquad \frac{4.4}{106.75} \times 100 = 4.12\%$$

ከላይ ካሉት የመረጃ ውጤቶች መገንዘብ እንደተቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ተማሪዎች በአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያስመዘገቡት የስህተት መጠን ያመለክታል። ምክንያቱም አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች 2.03% የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶችን ሲያስመዘግቡ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ 4.12% የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶችን በማስመዝገባቸው በጥናቱ ውጤት መሠረት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸው ተረጋግጧል። ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎች በፃፉት ድረሰት ውስጥ የሚታየውን የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ከፆታ አንፃር እንመለከት።

ሰንጠረዥ 13. የተጠኝ ተማሪዎች የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ከፆታ አንፃር የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ።

| የስህተት አይነት | የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች | ፆታ | የድርሰት ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአንቀጽ አደረጃጀት | አማርኛ አፍፊት | ወ | 6 | 1,140 | 190 | 19 | 3.17 | 1.7% |
| | | ሴ | 5 | 785 | 157 | 20 | 4 | 2.55% |
| | አማርኛ ኢ-ፍፊት | ወ | 16 | 1,865 | 116.56 | 64 | 4 | 3.43% |
| | | ሴ | 4 | 270 | 67.5 | 24 | 6 | 8.89% |

ከላይ በሰንጠረዥ 13 በቀረበው የጥናት ውጤት መሠረት ለመረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በየአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው ከአማርኛ ኢ-አፍፊቶቹ የተሻሉ መሆናቸውን ያመለክታል። በሌላ በኩል አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች 1.7% ያህል ስህተት ሲገጥማቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ደግሞ 3.43% ያህል ስህተት እንደተመዘገበባቸው የመረጃው ውጤት ያመለከታል። ከዚህ አኳያም አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች የተሻለ የአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል የሴት ተማሪዎችን ስህተት ስንመለከት አማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች 2.55% የሚሆን ስህተት ሲመዘገብባቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች 8.89% የሚሆን ስህተት ተመዝግቦባቸዋል። ከተመዘገበው የስህተት ድግግሞሽ አኳያም

አማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች የአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው የተሻሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከመረጃው ከተገኘው ውጤት በመነሳት አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻለ የአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 14. ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አደረጃጀትን በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት |
| ድርሰት ስጽፍ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቄ እጽፋለሁ | ፈጽሞ አልስማማም | 2 | 18.18% | 2 | 10% |
| | አልስማማም | 2 | 18.18% | 3 | 15% |
| | እስማማለሁ | 5 | 45.45% | 15 | 75% |
| | በጣም እስማማለሁ | 2 | 18.18% | 0 | 0% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 63.63% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደሚጽፉ የገለጹ ሲሆን 36.37% የሚሆኑት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደማይጽፉ የሰጡት መረጃ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 75% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደሚጽፉ የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 25% የሚሆኑት ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደማይጽፉ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆነ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣

ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደሚጽፉ መግለፃቸውን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየውን ተመሳሳይነት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 14 የሰጡት መረጃ ከኢ-አፍፊት ተማሪዎች አንፃር ተዓማኒነት አለው ለማለት ያስችላል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻለ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው በመፃፍ የተሻሉ መሆናቸውን ከጥናቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በዘፈቀደ ወይም መምህራንን ከመፍራት የመነጨ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

## 4.5. በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የታየ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም

አማርኛ ቋንቋ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩትን የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተቶችን በመቁጠር ከዚህ በታች በቀረበው መሠረት ትንተና ተሰጥቷል፡፡

ሰንጠረዥ 15. የተጠኚ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታየ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም በተመለከተ የሚያሳይ መረጃ፡፡

| የስህተት አይነት | አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፊደል ቅርጽ አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
| | 11 | 1,925 | 175 | 226 | 20.54 | 11.74% | 20 | 2,135 | 106.75 | 861 | 43.05 | 40.33% |

ከሰንጠረዥ 15. መመልከት እንደሚቻለው በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታየ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው 11 ድርሰቶች 1,925 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 226 ፊደላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው 20 ድርሰቶች 2,135 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 861 ፊደላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች የተመዘገበባቸው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ ስለሆነ የተሻለ የፊደላት አጠቃቀም ችሎታ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

እንዲሁም በተፃፉት ድርሰቶች ውስጥ የተፈጸመውን አማካይ የፊደላት ስህተት ለማወቅ የተቆጠረውን የፊደላት ስህተት ብዛት ከድርሰቶቹ ቁጥር ጋር በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያሉትን 226 የፊደላት ስህተቶች ለጠቅላላ ድርሰቶቹ (ለ11 ድርሰቶች) ስናካፍለው የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ በ20.54 ፊደላት ስህተት የተፃፈ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈልና በ100 በማብዛት የተመዘገበውን ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተችሏል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left| \; \frac{20.54}{175} \text{ X } 100 = 11.74\% \; \right|$$

በተጨማሪም ከሰንጠረዥ 15. መመልከት እንደሚቻለው በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታየ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው 20 ድርሰቶች 2,135 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 861 ፊዴላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል። እንዲሁም በተፃፉት ድርሰቶ ውስጥ የተፈጸመውን አማካይ የፊደላት ስህተት ለማወቅ የተቆጠረውን የፊደላት ስህተት ብዛት ከድርሰቶቹ ቁጥር ጋር በማካፈል ማወቅ ተችሏል።

በዚህም መሠረት አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያሉትን 861 የፊደላት ስህተቶች ለጠቅላላ ድርሰቶቹ (ለ20 ድርሰቶች) ስናካፍለው የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ በ43.05 ፊደላት ስህተት የተፃፈ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈልና በ100 በማብዛት የተመዘገበውን ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተችሏል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left| \; \frac{43.05}{106.75} \text{ X } 100 = 40.32\% \; \right|$$

ከላይ የተገኘው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፈትና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተመዘገቡት የፊደላት ስህተቶች ሲነፃፀሩ አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 11.74% ያህል የፊደላት አጠቃቀም ስህተት እንዳለባቸውና አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ደግሞ 40.32% ያህል ስህተት እንዳለባቸው የተገኘው ውጤት ያሳያል። ከዚህም አንፃር አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች አነስተኛ ስህተት

ስለተገኘባቸው በፊደላት አጠቃቀም ችሎታ የተሻሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የፊደላት አጠቃቀም ችሎታ ከፆታ አንፃር ስንመከት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ 16. የተጠኝ ተማሪዎች የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ችሎታ በፃፉት ድርሰት ከፆታ አንፃር የሚያሳይ መረጃ፡፡

| የስህተት አይነት | የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች | ፆታ | የድርሰት ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፊደል ቅርጽ አጠቃቀም | አማርኛ አፍፊት | ወ | 6 | 1,140 | 190 | 134 | 22.33 | 11.75% |
| | | ሴ | 5 | 785 | 157 | 92 | 18.4 | 11.71% |
| | አማርኛ ኢ-ፍፊት | ወ | 16 | 1,865 | 116.56 | 731 | 45.69 | 39.2% |
| | | ሴ | 4 | 270 | 67.5 | 130 | 32.5 | 48.15% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ ወንዶች 11.75% የፊደላት ስህተት ሲፈጽሙ ሴቶች 11.71% የፊዴላት ስህተት ተገኝቶባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃርም ሴቶቹ ከወንዶቹ ያስመገዘቡት ስህተት ትንሽ ስለሆነ በፊደላት አጠቃቀም ችሎታ የተሻሉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ ወንዶች 39.2% የፊደላት ስህተት ሲገጥማቸው ሴቶች 48.15% ተመዝግቦባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ወንዶቹ በፊደላት አጠቃቀም ችሎታ ከሴቶቹ የተሻሉ እንደሆኑ ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ከፊደላት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡

ሰንጠረዥ 17. የተጠኝ ተማሪዎች የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ችሎታን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ መረጃ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት |
| የምጽፈው ድርሰት ትክክለኛ የፊደል አጣጣል ይዞ የሚጓዝ ነው | ፈጽሞ አልስማማም | 1 | 9.09% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 2 | 18.18% | 1 | 5% |
| | እስማማለሁ | 4 | 36.36% | 17 | 85% |
| | በጣም እስማማለሁ | 4 | 36.36% | 2 | 10% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 72.72% የሚሆኑት ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደሚጠቀሙ 27.28% የሚሆኑት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደማይጠቀሙ በሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 85% የሚሆኑት ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 15% የሚሆኑት ደግሞ ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆኑ ኢአፍፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደሚጠቀሙ ጥናቱ ያሳየናል።

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየው ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 15 በቀረበው የድርሰታቸው መረጃ ውጤት መሠረት 11.74% የሚሆን የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተት ሲታይባቸው አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ በፃፉት ድርሰት 40.33% የሚሆን የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተት ታይቶባቸዋል።

በመሆኑም የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ የሚጽፉት የፊደላት ቅርጽ ትክክል ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። ስህተታቸውንም እንዲያውቁ የመምህራን ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቻቸው ተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ በማድረግ ማስተካከያ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል። ከዚህ አንፃር የተሰጠው ምላሽ ከድርሰቶቻቸው ጋር ተያዥነት ያለውና ተገቢ ነው ማለት አይቻልም።

ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የፊደላት አጠቃቀም አጠቃቀም ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማስረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል። በአረፍተ- ነገሮቹ ውስጥ ጉላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም። በመሆኑም በጥናቱ መጨረሻ በምሳሌነት አጥኚው የተጠቀማቸውን አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በአባሪ "መ" ላይ እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎችን የፃፉትን ድርሰት በአባሪ "ሠ" ላይ ከጥናቱ ጋር ተያይዘው ይገኛሉ።

## 1. አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የፊደላት ስህተቶች

- "የጋሞባለ፣ ትለቅ፣ እግ በጣም፣ መጠጤብሞ፣ በሀላ፣ ናቅም፣ ለበልጋ መስሪያ፣ አብዛሀኛውን፣ የሚናገኝው፣ የሞጣሉ፣ ቢተገኝ እና ወዘተ…"

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት ቃላት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች በፀፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በተገኙ ቃላት የታዩ የፊደላት ግድፈቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ግድፈቶች ወይም ስህተቶች የተፈጠሩት ተማሪዎቹ ፊደላትንና አጠቃቀማቸውን በአግባቡ ለይቶ ካለማዎቅ የመጣ መሆኑን ከስህተቶቹ ማወቅ ይቻላል፡፡ በምሳሌዎቹ ከቀረቡት ውስጥ ከሁለቱ ቃላት ማለትም "አብዛሀኛውን" እና "ለበልጋ መስሪያ" ከሚሉት ቃላት በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ፊደላትንና አጠቃቀማቸውን በአግባቡ ለይቶ ካለማዎቅ የመጣ ችግር ነው፡፡ "አብዛሀኛውን" እና "ለበልጋ መስሪያ" የሚሉት ቃላት ግን ከዘዬ ወይም ከቀበለኛ ቋንቋ አጠቃቀም ተጽዕኖ የመጣ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በምሳሌነት የቀረቡትን ቃላት ከፃፉት ድርሰት አውድ አንፃር ምን ለማለት ፈልገው እንድህ እንደፃፉ ከዚህበታች በፃፉት ቃላት ቅንፍ ውስጥ ተቀምጧል፡፡

- "የጋሞባለ (ጋምቤላ)፣ ትለቅ (ትልቅ)፣ እግ በጣም (እጅግ በጣም)፣ መጠጤብሞ (ማጠቢያም)፣ በሀላ (በኋላ)፣ ናቅም (ጥቅም)፣ ለበልጋ መስሪያ (ለአልጋ መስሪያ)፣ አብዛሀኛውን (አብዛኛውን)፣ የሚናገኝው (የምናገኘው)፣ የሞጣሉ (የሚጣሉ)፣ ቢተገኝ (በተገኝ) እና ወዘተ…"

## 2. ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የፊደላት ስህተቶች

- "የምመጡ፣ ልውል፣ ቡዙ ፣ ከፎውን ፣ ሐዛብ፣ ግዜ ፣ ምጠቀም ፣ ውንዝ ፣ የሞያጠና ፣ የሞያነብ ፣ የጋምበለ ፣ወሶጥ ፣ሁለ ፣ ደር ፣መንጎ ፣ መኖ "

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት ቃላት አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በፀፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በተገኙ ቃላት የታዩ የፊደላት ግድፈቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ግድፈቶች ወይም ስተቶች የተፈጠሩት ተማሪዎቹ ፊደላትንና አጠቃቀማቸውን በአግባቡ ለይቶ ካለማዎቅ የመጣ ብቻ አለመሆኑን ከስህተቶቹ ማዎቅ ይቻላል፡፡ ይህም ችግር ሊፈጠር የቻለው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የመጣ ችግር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በምሳሌነት የቀረቡትን ቃላት ከፃፉት ድርሰት አውድ አንፃር ምን ለማለት ፈልገው እንድህ እንደፃፉ ከዚህበታች በፃፉት ቃላት ቅንፍ ውስጥ ተቀምጧል፡፡

- "የምመጡ፣ (የሚመጡ) ልውል (ሊውል)፣ ቡዙ (ብዙ)፣ ከፎውን (ክፉውን)፣ ሐዛብ (ሕዝብ)፣ ግዜ (ጊዜ)፣ ምጠቀም (መጠቀም)፣ ውንዝ (ወንዝ)፣ የሞያጠና (የሚያጠና)፣ የሞያነብ (የሚያነብ)፣ የጋምበለ (ጋምቤላ)፣ ወሶጥ (ውስጥ)፣ ሁለ (ሁሉ)፣ ደር (ዳር)፣ መንጎ (ማንጎ)፣ መኖ (መኖር) "

## 4.6. ተማሪዎች ለጽሕፈት ችሎታ ያላቸው ፍላጎት

ተማሪዎች የጽህፈት ችሎታን ለማዳበር ከሚያስችላቸው ነገሮች ውስጥ የመጀመሪያው ለጽህፈት ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ነው፡፡ በመሆኑም ለጽህፈት ትምህርት ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ ያስችላሉ ተብለው በጽሑፍ መጠይቁ ውስጥ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ 18. ተጠኝ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፌት | አማርኛ አፍፌት | አማርኛ ኢ-አፍፌት | አማርኛ ኢ-አፍፌት |
| የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት አለኝ | ፈጽሞ አልስማማም | 0 | 0% | 2 | 10% |
| | አልስማማም | 1 | 9.09% | 1 | 5% |
| | እስማማለሁ | 7 | 63.63% | 10 | 50% |
| | በጣም እስማማለሁ | 3 | 27.27% | 7 | 35% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፌት ተማሪዎች ውስጥ 90.9% የሚሆኑት የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹ ሲሆን 9.09% የሚሆኑት አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች ደግሞ የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንደሌላቸው የሰጡት መረጃ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች ውስጥ 85% የሚሆኑት የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 15% የሚሆኑት ደግሞ የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንሌላቸው የተገኘው የጥናት ውጤት ያሳያል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፌትም ሆኑ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው መግለፃቸውን ከጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየውን ይገልፃል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹት በፍላጎታቸው የትምህርት ክፍሉን ስለመረጡት እና ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ድርሰት የመፃፍ ፍላጎት ያለው ተማሪ በመረጠው ርዕስ ሰዎችን ሊያግባባ የሚችል ጽሑፍ ይጽፋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የፃፉት ድርሰት ግን ይህን አያሳይም፡፡

## 4.7. መምህራን ለጽሕፈት ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት

ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የተሻለ ችሎታ እንዲኖራቸው በግላቸው ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ መምህራኖቻቸው ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቹን ይደግፉ እንደሆን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሰንጠረዥ 19. ተጠኝ ተማሪዎች መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጣሉ ተብለው ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፈት | አማርኛ አፍፈት | አማርኛ ኢ-አፍፈት | አማርኛ ኢ-አፍፈት |
| መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጣሉ | ፈጽሞ አልስማማም | 2 | 18.18% | 4 | 20% |
| | አልስማማም | 4 | 36.36% | 4 | 20% |
| | እስማማለሁ | 4 | 36.36% | 6 | 30% |
| | በጣም እስማማለሁ | 1 | 9.09% | 6 | 30% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ውስጥ 54.54% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ማስተካከያና ግብረ-መልስ እንደማይሰጧቸው የገለጹ ሲሆን 45.45% የሚሆኑት አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው

የጽሑፍ መጠይቅ ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደሚሰጧቸው የሰጡት መረጃ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 60% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደሚሰጧቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 40% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደማይሰጧቸው  የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆነ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደማይሰጧቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመሆኑም የጥናቱ ውጤት የሚያሳየን መምህራን የጽህፈት ትምህርት በተግባር እንደማያስተምሯቸው ወይም ቢያስተምሯቸውም ለሰጡት መልመጃ ተገቢውን ማስተካከያ እንደማይሰጡ ነው፡፡ ይህም ደግሞ የጽህፈት ትምህርት ክሂል ስለሆነ ተማሪዎቹ በተግባር እንዲማሩት ካላደረግንና ለስህተታቸው ተገቢውን ማስተካከያ ካልተሰጣቸው የጽህፈት ክሂልን ሊያዳብሩ አይችሉም፡፡ ቀጥለን ደግሞ ይህንኑ መረጃ የሚያጠናክርልንን የተጠኝ ተማሪዎችን ምላሽ እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 20. ተጠኝ ተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት | አማርኛ ኢ-አፍፊት |
| የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው | ፈጽሞ አልስማማም | 4 | 36.36% | 4 | 20% |
| | አልስማማም | 4 | 36.36% | 11 | 55% |
| | እስማማለሁ | 3 | 27.27% | 5 | 25% |
| | በጣም እስማማለሁ | 0 | 0% | 0 | 0% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 72.72% የሚሆኑት ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ መምህሩ እንደሚመርጥላቸው የገለጹ ሲሆን 27.27% የሚሆኑት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ደግሞ ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ መምህሩ እንደማይመርጥላቸው የሰጡት መረጃ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ውስጥ 75% የሚሆኑት ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ መምህሩ እንደሚመርጥላቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 25% የሚሆኑት ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ መምህሩ እንደማይመርጥላቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍፊትም ሆኑ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ የድርሰት ርዕስ በራሳቸው እንደማይመርጡ እና በመምህራን አስገዳጅነት ርዕስ እንደሚሰጣቸው ጥናቱ ያመለክተናል፡፡

በመሆኑም የጽህፈት ክሂልን ይበልጥ ለማዳበር ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት ርዕስ ቢመርጡ የሚያውቁትን ነገር መነሻ ስለሚያደርጉ ድርሰቱን ለመፃፍ የሀሳብና የቃላት ችግር አይገጥማቸውም፡፡ ምክንያቱም ከሚያውቁት ነገርና ከፍላጎታቸው የመነጨ ስለሚሆን ብዙ አይቸገሩም፡፡ ነገር ግን በመምህሩ የሚመረጥላቸው ከሆነ ያለፍላጎታቸው ስሚጽፉ የሀሳብና የቃላት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ ከዚህም በላይ የጽህፈት ትምህርትን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም መምህሩ በጽህፈት ትምህርት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ ቢያደርግ የተሻለ ነው፡፡ ነገር ግን የድርሰት ርዕስ በተማሪዎች ይወሰን ማለት ሳይሆን ክሂሉን እያዳበሩ ሲመጡ በመምህሩ በሚሰጣቸው ርዕስ ለመፃፍ ብዙም አይቸገሩም፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዓቢይ አላማ ስር ለተነሱት አምስት ንዑስ አላማዎች እና በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ ለተጠቀሱት ሁለት መሠረታዊ የምርምር ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው፡፡

በመሆኑም የምርምሩ ንዑስ አላማዎች ድርሰት ሲጽፉ የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን መመርመር፤ በቋንቋው ህጎች /ስዋሰው/ የመጠቀም ችሎታቸው ምን ላይ እንደሚገኝ መገምገም፤ ድርሰት ሲጽፉ ከፆታ አንፃር ያለውን ልዩነት መገምገም፤ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ፤ እንዲሁም በአጠቃላይ በጽሑፍ ክሂል ላይ ያላቸውን ፍላጎትና ልምድ ማጥናት እንዲሁም ከአማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችግር በየትኞቹ ተማሪዎች ላይ ይሰተዋላል? በጽህፈት ችሎታቸውስ የትኞቹ ይሻላሉ? ለሚሉት በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ ለተጠቀሱት ሁለት መሠረታዊ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ በተካሄደው ጥናት የሚከተለውን የጥናት ውጤት አስገኝቷል፡፡

የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች የተመዘገበባችው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ ስለሆነ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው በጥናቱ ለማወቅ ተችሏ፡፡ እንዲሁም በአጠቃላይ አማርኛ አፍፊትም ይሁኑ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከሴቶቹ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው በሁለቱም ፆታዎች መካከል የተደረገው የጥናት ውጤት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ይህን ጥናት ቀደም ሲል ከተጠኑ ጥናቶች የሚለየው በቃላት አጠቃቀም ወንዶች ተሽለው መገኘታቸው ነው፡፡ የቀደምት ጥናቶቶች ግን በቃላት አጠቃቀም ሴቶች እንደሚሻሉ አሳይተዋል፡፡

በተጨማሪም ከጥናት ውጤቱ መረዳት እንደተቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ተማሪዎች በሰዋስዋዊ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ በጥናቱ ያስመዘገቡት ውጤት ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በአጠቃላይ ከመረጃው ከተገኘው ውጤት

በመነሳት አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች በሁለቱም ፆታዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የተሻለ የአረፍ-ተነገር አወቃቀር ችሎታ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በቃላት አጠቃቀምና በአረፍተ-ነገር አወቃቀር በጣም ችግር እንዳለባቸው የተደረገው ጥናት ውጤት ያመለክታል፡፡

ነገር ግን በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀምን በተመለከተ ከጥናት ውጤቶች መገንዘብ እንደተቻለው በጠቅላላ ድምር ውጤት አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ከአፍፊት ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀምን በሁለቱም ፆታዎች መካከል በተካሄደው ጥናት አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከአማርኛ ኢአፍፊት ወንድ ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡ እንዲሁም በሴት ተማሪዎች መካካል በተደረገው ጥናት አማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች ከአማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ የተገኘው ውጤት ይበል የሚያስብል ቢሆንም አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ላይም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል፡፡

በአንቀጽ አደረጃጀትና አጠቃቀም በተደረገው የጥናት ውጤት መገንዘብ እንደተቻለው አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ተማሪዎች በአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያስመዝገቡት የስህተት መጠን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በሁለቱም ፆታዎች መካከል በተካሄደው ጥናት አማርኛ አፍፊት ወንድ ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ወንድ ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በሴት ተማሪዎች መካካል በተደረገው ጥናት አማርኛ አፍፊት ሴት ተማሪዎች ከአማርኛ ኢ-አፍፊት ሴት ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በፊደላት ቅርጽ አጣጣልና አጠቃቀም በተደረገው ጥናት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች አነስተኛ ስህተት ስለተገኘባቸው የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እንድሁም በሁለቱም ፆታዎች በተደረገውም ጥናት አማርኛ አፍፊት ተማሪዎች ከኢ-አፍፊት ተማሪዎች በሁለቱም ፆታ የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ እንድህ የሆነበት ምክንያት በተለይ አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በከፍተኛ ሁኔታ ተጽዕኖ እንዳደረገባቸው በተግባር ከፃፉት ድርሰት ለማዎቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም በተማሪዎች የድርሰት ጽህፈት ፍላጎትና መምህራን ለጽህፈት ትምህርት በሚሰጡት ትኩረት ላይ በተደረገው ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት እንዳላቸው ከተደረገው ጥናት ውጤት ማወቅ ተችሏ፡፡ ነገር ግን ፍላጎት ብቻውን

ስኬት አይሆንም። የጽህፈት ትምህርት በተግባር የተደገፈ፣ ተከታታይ የሆነ እና ተግባርነቱ የበዛ እንዲሁም የመምህራንን ክትትልና ምግበ ምላሽ የሚጠይቅ ነው። ሆኖም ከጥናቱ የተገኘው ውጤት መምህራን ለክሂሉ ትኩረት ሰጥተው እንደማያስተምሩ እና ቢያስተምሩም ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት በራሳቸው ፍላጎት የሚመርጡት ርዕስ ሳይሆን በመምህራኑ እደሚመረጥላቸው ጥናቱ ይጠቁማል። በተጨማሪም ተማሪዎች ለፃፉት ድርሰት መምህራኑ ወዳውኑ ምግበ ምላሽ እንደማይሰጧቸውና ስህተታቸውን አውቀው ለወደፊት የተሻሉ ሆነው ለመገኘት የሚያስችላቸው ሁኔታ እንደሌለ በጥናቱ ተረጋግጧል።

## 5.2 አስተያየት

የጽህፈት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረትን ከሚጠይቁ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ነው። በመሆኑም ተማሪዎች ይህን ክሂል በአግባቡ እንዲያዳብሩትና ተገቢውን እውቀት እንዲጨብጡ በመማር ማስተማሩ የሚደረገው የመምህራን ድጋፍና ክትትል በማያቋርጥ ሁኔታ መተግበር ቢችሉ የተሻለ ነው።

በመሆኑም አማርኛ አፍፈትም ሆነ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን በከፍተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ላይ የሚያዳብሩት ሳይሆን ከታች ከዝቅተኛ ደረጃ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ መምህራን ለዚህ ትምህርት ትኩረት ሰጥተው፣ በእቅድና በተደራጀ መልኩ የፊደላትን ስርዓት፣ የስርዓተነጥቦችን አጠቃቀም፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የመሳሰሉትን ለተማሪዎቻቸው ማስተማር ሲችሉ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማዳበር በምን አይነት መንገድ ትምህርቱ ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል? የሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት ቢሰጡበት የተሻለ ይሆናል። ተማሪዎቹ ምን አይነት ተግባራትን ቢያከናውኑ የመፃፍ ክሂላቸውን ያዳብራሉ? የሚሉት ጉዳዮች ላይ በደንብ መስራቱ ተገቢ ነው። እንዲሁም ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂላቸው ለሚፈጽሙት ስህተት እንዴት መረዳት እንዳለባቸውና ስህተታቸውን እንዴት ማስተካከል እንደሚገባቸው መምህራን ድጋፍ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል።

ስለሆነም በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የሚያሳየን ተማሪዎቹ በተለያየ የጽህፈት ክሂል የተለያዩ ደረጃ ላይ እንዳሉ ነው። ለምሳሌ በቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍፈት ተማሪዎች የተሻሉ ሲሆኑ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ከአፍፈት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ አመልክቷል።

እንዲሁም ሁለቱም ቡድኖች ያላቸውን የክሂል ክፍተት እንዲያጠቡ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ድጋፍና ክትትል ቢያደርግ የተሻለ ይሆናል፡፡ ይሄውም መምህሩ ተማሪዎች የግልና የቡድን ስራ እንዲሰሩ በማድረግ አንዱ ተማሪ ከሌላው እየተማረ የክሂል እውቀት ክፍተታቸውን የሚሞሉበትን መንገድ ማመቻቸት አንዱና ተመራጭ መንገድ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ጫና ሳይፈጥሩ ተማሪዎቹ በፈለጉት ርዕስ ላይ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግና ድርሰቶችን አይተው ችግራቸውን እንዲቀርፉ ግብረ-መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህን ክፍተት መምህራኑ እያጠበቡና እየቀረፉ ካልሄዱ የተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂል ክፍተት አብሯቸው ይጓዝና መምህር ከሆኑ በኂላ በአሁኑ ሰዓት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየታየ ያለውን የመፃፍ ችግር ከማቃለል ይልቅ ወደ ማባባሱ ይሄድና ትውልድ ገዳይ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተማሪዎች ተመርቀው ወደ መምህርነቱ ሲቀላቀሉ በአንደኛ ደረጃ መምህርነት ስለሚሰማሩና ይህም የትምህርት ደረጃ ለቀጣዩም የትምህርት ደረጃ መሠረት ስለሆነ የመምህራን ኮሌጁና የትምህርት ክፍሉ መምህራን በጋራ ችግሩ የሚቀረፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ መሆኑን የጥናቱ አቅራቢ ያመላክታል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሰይድ ይመር። (1993)። "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ *መማሪያ መጽሐፍ* የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነዘዴ ትግበራ"። አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር፣ (ያልታተመ)።

በድሉ ዋቅጅራ። (2007)። *በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር።* (ሁለተኛ እትም)፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ባየ ይማም። (2000)። *የአመርኛ ሰዋስው።* የተሻሻለ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.መኅበር።

ተስፋዬ ሸዋዬ። (1981)። "ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር"። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)።

አለማየሁ ተመስገን። (1998)። "አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁለት የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት"። አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር፣ (ያልታተመ)።

አማረ ማሞ። (1986)። *የልብወለድ ድርሰት አፃፃፍ መሠረታዊ መመሪያ።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ኢሳያስ ይልማ። (2002)። "የጽሑፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት አደረጃጀታቸው 10+2 የሁኑ ተማሪዎች በአማርኛ ደብዳቤ ለመፃፍ ያላቸው ብቃት በጎባና ሮቤ መሰናዶ ትምህርት ቤት ናሙናነት"። አዲስ አበባ፣በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር፣ (ያልታተመ)።

ያለዉ እንዳወቅ። (2001)። *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።* (ሁለተኛ እትም)፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጌታቸው ቸርነት። (2001)። "በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት"። አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር፣ (ያልታተመ)።

Abiy Y. (2013). *High School Students' Writing Skills and their English Language Proficiency as Predictors of their English Language Writing Performance.* Bahir Dar University, Faculty of Humanities, Department of English, Ethiop. J. Educ. & Sc. Vol. 9 No. 1 September 2013.

*Byrne, D. (1991). Teaching Writing Skills. London: Longman Group, UK limited.*

Celece-Murcia, M. (2001). *Teaching English as Second or Foreign Language*. (3rd ed.), Boston: Heinle and Heile Publishers.

Creswell, J. W. (2009). *Research Design, Qualitative, Quantitative, & Mixed Method Approaches.* (3rd Ed), University of Nebraska-Lincoln.

Davies, A. and Widdowson. H. G. (1974). "Reading and Writing". In J.P.B. Allen & S.Pit Corder (eds.), The Edinburgh Course in Applied Lingustics. Vol.3 (PP. 155-188), London: Oxfor University Press.

Harmer, J. C. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* London: Longman Group, UK limited.

____________. (1994). *Teaching and Learning Grammer.* London: Longman Group, UK limited.

Heaton, J. B. (1990). *Writing English Language Tests.* (3rd Edition), London: Longman Group, UK limited.

Hedge, T. (1988). *Writing.* Oxford: Oxford University Press.

Hughes, A. (2003). *Testing for Language Teaching.* (2nd Edition), United Kingdom: Cambridge University Press.

Kamrul, Md. H. and Mohd. M. A. (2010). *Approaches to Writing in EFL/ESL Context:Balancing Product and Process in Writing Class at Tertiary Level.* Journal of NELTA Vol. 15 No. 1-2 December 2010

Kenworthy, R. (2006). *TESL/EJ Teaching English as a Second or Foreign Language*. (Volume 10 Number 1), Ohio University, Hong Kong.

Kroll, B. (1990). ‘‘What Does Time Buy ? ESL Student Performance on Home Versus Class Composition’’ In B. Kroll (ed) Second Language Writing Research insights for the Class room . (PP. 57-68), Cambridge: Cambridge University Press.

Norrish, J. (1990). *Language Learners and their Errors.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Nunan, D. (1989). *Designing Tasks for the Communicative Classroom.* Cambridge: Cambridge University Press.

Pincas, A. (1982). *Teaching English Writing.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Raimes, A. (1983). *Techniques in Teaching Writing.* Oxford: Oxford University Press.

Richards, J. C. (1990). *The Language Teaching Matrix.* Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J and Renandya, A. (2002). *Methodology in Language Teaching An Anthology of Current Practice.* Cambridge: Cambridge University Press.

Staples, S. and Randi, R. (2016). *Understanding First-year L2 Writing: A lexico-grammatical analysis across L1s, genres, and language ratings.* Journal of Second Language Writing 32 (2016) 17–35 2016 Elsevier Inc. All rights reserved.

Trimmer, J. and James, M. (1988). *Writing with Purpose.* Boston: Houghton Mifflin Company.

Ur, P. (1996). *A Cource in Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Zamel, V. (1985). “Responding to Student Writing” TESOL Quarterly. 191, (PP.79-101).

# አባሪዎች

## አባሪ “ሀ”

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

# ለድህረ-ምረቃ ምርምር በተማሪዎች የሚሞላ የምርምር ጥያቄዎች

# በሁለተኛ አመት የኮሌጅ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

## ክፍል አንድ

## ውድ ተማሪዎች፡-

የዚህ መጠይቅ ዓላማ፡- በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል በሚማሩ ሁለተኛ አመት አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ላይ በማተኮር በጽህፈት ክሂል ችሎታ የትኞቹ ተሸለው እንደሚገኙ በማነፃፀር ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ፤ ችግሩን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብና ተማሪዎቹ ተመርቀው ወደ ማስተማሩ ሲሰማሩ በራሳቸው ላይ የሚታየውን ችግር በመቅረፍ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎቻቸውን የጽህፈት ችግር መቅረፍ የሚያስችላቸውን መንገድ መጠቆም ነው፡፡

ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባችሁ ተገቢውን መልስ በመመለስ ቀና ትብብራችሁን እንድታደርጉ ትጠየቃላችሁ፡፡ በመሆኑም ውድ የሆነውን የትምህርት ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

### ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም አይፃፍም
2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**አጠቃላይ መረጃ**

**II, ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ**

1. ፆታ________________________________________
2. የትምህርት ደረጃ________________________________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ______________________________

**ክፍል ሶስት**

**III, ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የቀረቡት ጥያቄዎች አራት አማራጮችን ይዘዋል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ነው የምትሉትን በመምረጥ በሳጥኑ ውስጥ "X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ፡፡**

1. ፈጽሞ አልስማማም
2. አልስማማም
3. እስማማለሁ
4. በጣም እስማማለሁ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርት ክፍሉ መምህራን በጽህፈት ወቅት ስለምጠቀምባቸው የተለያዩ የቃላት ምርጫ አስተምረውኛል | | | | |
| 2 | ድርሰትን ስጽፍ ሰዋስውን በአግባቡ እጠቀማለሁ | | | | |
| 3 | የትምህርት ክፍሉ መምህራን ስለአማርኛ ስርዓተነጥቦችና አጠቃቀም አስተምረውኛል | | | | |
| 4 | ድርሰት ስጽፍ የአንቀጽ አንድነት፣ ተለጣጣቂነትንና ጉልህነትን ጠብቄ እጽፋለሁ | | | | |
| 5 | የምጽፈው ድርሰት ትክክለኛ የፊደል አጣጣል ይዞ የሚገኝ ስለሆነ አንባቢዎቼ ሳይቸገሩ ያነቡታል | | | | |
| 6 | የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት አለኝ | | | | |
| 7 | የትምህርት ክፍሉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጣሉ | | | | |
| 8 | የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልን መምህሩ ነው | | | | |
| 10 | ድርሰትን ስጽፍ ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀምና ስርዓተነጥቦችን በአግባቡ እጠቀማለሁ | | | | |

## አባሪ "ለ"

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

# ለድህረ-ምረቃ ምርምር በተማሪዎች የሚሞላ የምርምር ጥያቄዎች

# በሁለተኛ አመት የኮሌጅ ተማሪዎች የሚፃፍ ድርሰት

## ክፍል አንድ

## ውድ ተማሪዎች፡-

ይህ የድርሰት ርዕስ ዓላማ፡- በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል በሚማሩ ሁለተኛ አመት አማርኛ አፍፊትና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ላይ በማተኮር በጽህፈት ክሂል ችሎታ የትኞቹ ተሽለው እንደሚገኙ በማነፃፀር ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ፤ ችግሩን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብና ተማሪዎቹ ተመርቀው ወደ ማስተማሩ ሲሰማሩ በራሳቸው ላይ የሚታየውን ችግር በመቅረፍ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎቻቸውን የጽህፈት ችግር መቅረፍ የሚያስችላቸውን መንገድ መጠቆም ነው፡፡

በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የቀረቡት የድርሰት ርዕሶች በየጊዜው ከሚሰጡት የክፍል ውስጥ ፈተናዎች ወይም በመንፈቅ-ዓመቱ መጨረሻ ከሚሰጡት የማጠቃለያ ፈተናዎች ጋር ግንኙነት የሌላቸው ስለሆነ ውጤቱ አይያዝም ወይም ከተፈተናችሁትም ሆነ ወደፊት ከምትፈተኑት ፈተናዎች ውጤት ጋር አብሮ አይደመርም፡፡ ስለዚህ ምንም አይነት ስጋት ሳይኖራችሁ በነፃነትና ትኩረት በመስጠት በትዕዛዙ መሠረት ከዚህ በታች ለቀረቡት የድርሰት ርዕሶች በምትጽፉት ድርሰት ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- 1. በመጠይቁ ላይ ስም አይፃፍም

2 መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## አጠቃላይ መረጃ

**II, ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ**

1. ፆታ________________________________________
2. የትምህርት ደረጃ ________________________________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ______________________________

## ክፍል ሁለት

**III, ከዚህ ቀጥሎ አስር የድርሰት ርዕሶች ቀርበዋል፤ ከአስሩ ውስጥ ይበልጥ ሀሳባችሁን ልትገልጹበት የሚያስችላችሁን ርዕስ በመምረጥ 150-350 በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ፃፉ፡፡**

1. የባሮ ወንዝ ጥቅም
2. ዘመናዊ እርሻ በጋምቤላ
3. የበረሃ አስቸጋሪነት
4. የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች
5. የማንጎ ጥቅም
6. የጋምቤላ መምህራን ኮሌጅ
7. የዛፍ ጥቅም
8. የሀገር ፍቅር
9. የጓደኛ ታማኝነት
10. የጎበዝ ተማሪ ተግባር

# አባሪ "ሐ"

## የድርሰት እርማት መስፈርት

### ውድ መምህራን

ከዚህ በታች የተሰጠውን የእርማት መስፈርት ትርጉም በመጠቀም በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች ለይታችሁ በማውጣት የስህተቶቹን አይነትና ብዛት በተዘጋጀው ቅጽ ላይ አስፍሩ፡፡ በመሆኑም ውድ ባልደረቦቼ የተጣበበ ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

### የማረሚያ መስፈርት ትርጉም

1. **የቃላት አጠቃቀም ስህተት**
   - 1.1 የቃላት ድግግሞሽ
   - 1.2 የቃላት ድረታ
   - 1.3 ባዕድ ቃላት

2. **ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ስህተት**
   - 2.1 የቁጥር ስህተት
   - 2.2 የመደብ አጠቃቀም ስህተት
   - 2.3 የቃላት ቅደም ተከተል ስህተት
   - 2.4 የቅጥያ አጠቃቀም ስህተት

3. **የአንቀጽ አወቃቀር ስህተት**
   - 3.1 የአንቀጽ ጉልህነት አለመኖር
   - 3.2 የአንቀጽ መሸጋገሪያ አጠቃቀም ስህተት
   - 3.3 የአንቀጽ አንድነት
   - 3.4 የአንቀጽ ተያያዥነት

## 4. ስርዓተ-ነጥቦችን በአግባቡ አለመጠቀም

4.1 አራት ነጥብ

4.2 ነጠላ ሰረዝ

4.3 ትምህርተ ጥቅስ

4.4 የጥያቄ ምልክት

## 5. ትክክለኛ የድርሰት ቅርጽና የፊደላት ቅርጽ አለመጠቀም

5.1 ትክክል ያልሆኑ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም

5.2 የህዳግ አጠቃቀም ስህተት

5.3 ፊደል ግድፈትና ጭመራ

5.4 ስርዝ ድልዝ

# አባሪ “መ”

## አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች የፃፉት ድርሰት ናሙናዎች

# አባሪ “ሠ”

## አማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የፃፉት ድርሰት ናሙናዎች

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜና ፊርማዬን ያስቀመጥኩት የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ማስተማር ስነ-ዘዴ የድህረ-ምረቃ ተማሪ ስሆን ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች በትክክል የተጠቀምኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ___ሁሴን አህመድ ሁሴን___

ፊርማ ______________

ቀን ___16/10/2009 ዓ.ም.___